ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 282 ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## 2 ነጥብ 8 በመቶ የነበረው የከተማዋ የደን ሽፋን በአረንጓዴ ዐሻራው 15 በመቶ ደርሷል

ልጅዓለም ፍቅሬ



አዲስ አበባ፡- ሁለት ነጥብ ስምንት በመቶ የነበረውን የአዲስ አበባ የደን ሽፋን በተደረገው የአረንጓዴ ዐሻራ ልዩ ርብርብ ባለፉት አራት ዓመታት 15 በመቶ ማድረስ መቻሉን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ ሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ የማስጀመሪያ መርሃ-ግብር ትናንት ተካሂዷል፡፡

በማስጀመሪያ መርሃ- ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ ከተማዋ ከነበራት ሁለት ነጥብ ስምንት በመቶ የደን ሽፋን ባለፉት አራት ዓመታት የአረንጓዴ ዐሻራ የማኖር ልዩ ርብርብ ወደ 15 በመቶ ማሳደግ ተችሏል ብለዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች በዘንድሮው ክረምት ነገን ዛሬ እንትከል በሚል መርህ በከተማው የሚከናወነውን 17 ሚሊዮን ችግኝ የመትከል መርሃግብር በይፋ አስጀምረዋል፡፡

እንደ አገር በአንደኛው ምዕራፍ 25 ቢሊዮን ችግኝ በመትከል የተቀመጠውን ግብ ማሳካት ተችሏል ያሉት ከንቲባዋ፤ በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃም 41 ሚሊዮን

2 ነጥብ 8 በመቶ የነበረው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ፖለቲከኞች በኃላፊነት ሊሰሩ ይገባል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ፖለቲከኞች በኃላፊነትና ከሕጋዊ ሥርዓት ባልወጣ መንገድ ሊሰሩ እንደሚገባ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም፣ ዕድገት እና ልማትን ማምጣት የሚቻለው እያንዳንዱን ተግባር በኃላፊነት እና በሕጋዊ ሥርዓት ማከናወን ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ፖለቲከኞች በኃላፊነት ሊሰሩ ይገባል፡፡

ፖለቲከኞች ፖለቲካቸውን በኃላፊነትና በሕጋዊ መንገድ ማራመድ ይኖርባቸዋል ያሉት ዶክተር መብራቱ፤ በዚህም በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ከማስፈን ባለፈ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር መብራቱ ገለጻ፣ ፖለቲከኞች በኃላፊነትና



ዶክተር መብራቱ አለሙ

በሕጋዊ መንገድ ካልሰሩ ጽንፈኝነትን ሊያከስትል ይችላል፡፡ ጽንፈኝነት እኔ የበላይ፤ ፍጹም እና ትክክል ነኝ በሚል የሌላውን ሃሳብ የማይቀበልና የማያከብር



አቶ መልካሙ ሹምየ

ነው፡፡ ይህም ማህበራዊ ግንኙነት እንዳይኖር፣ አገር እንዲረበሽ፣ ኢኮኖሚያዊ እድገት እንዳይኖር እና

ዘላቂ ሰላምን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







## ዩኒቨርሲቲዎች የዩኒቨርሲቲ መውጫና የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ለመስጠት እየተዘጋጁ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ዩኒቨርሲቲዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እና የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናን ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ገለጹ።

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር መገርሳ ቃሲም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የ12ኛ ክፍል መውጫ ፈተናን በተሟላ መልኩ ለመስጠት የሚያስችለውን አቅም ከአምናው ልምድ በመቅሰም የዘንድሮውን ፈተና በብቃት ለመወጣት በርካታ የዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በዚህም ለተፈታኝ ተማሪዎች ምቹ አገልግሎት ለመስጠት የምግብ፣ የጤና እና የመሰረተ ልማት ጉዳዮች

ዩኒቨርሲቲዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



### የቀላል ባቡር ትራንስፖርት የመዘግየትና ከልክ በላይ የመጫን ችግር አለበት

ገጽ 3






# ስተሻለ ውጤት የቅድመ ፈተና ትጋት

**ዳግማዊት ግርማ**



ያለንበት ዘመን እውቀት ግድ የሚልበት ነው። ሳይንስና ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ሁኔታ ባደገበት በዚህ ዘመን ከትምህርት ውጭ ተወዳዳሪ ሆኖ መኖር አዳጋች ነው። አገራት ኩራታቸው ምንጩ የተማረ የሰው ኃይላቸው ነው፡፡ የሰውኛ ቋንቋ መግባቢያ የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም የመኖር ድንቅ ቅኔ ነው መማር። መማር ሰው መሆን ይመተርበታል፤ ከልክ የሚልቅ ከመለኪያ በላይም ጭምር፡፡

የሰው ልጅ ራሱን በዛሬ ሥልጣኔ የቃኘው በእውቀት አሻጋሪነት ነው፡፡ ሥልጣኔ ልኩ የሚፈተነው በአዋቂዎች ብዛት ነው፡፡ ሰው በመሆን ልኬት ውስጥ መማር የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል፡፡ መማር የአለቃን ቁጥር ቀንሶ የራስ ገዢ መሆኛ ሁነኛ መላ ነው፡፡

በዚህ የእውቀት ዳና ተጓዥ ሁሉ እልፍ መሰናክሎችን ያልፋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ደጅ ማንኳኳትም ግዴታው ነው፡፡ ይህ የተቋማቱ በር የሚከፈተው ደግሞ ቤቱን ለሚመጥኑ እንኳኪዎች ብቻ ነው፡፡ ባሳለፍነው ዓመትም ተዓምር የሚመስል ክስተት ተፈጠረ፡፡ በዚህም ስንዴ ከእንክርዳድ ተለየ፡፡ ከአንድ ሺህ የሚልቁ ተቋማት ተማሪዎች የኀዘን ካባ ደረቡ። እነዚህ ልጆች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ደጃፍ ለመርገጥ ናፍቀዋልና፡፡

አሁን በያዝነው ዓመትስ ተቋማትን የፈተና ዝግጅት ነገር እንዴት አድርጓችኋል ልንል ወደድን፡፡ በዚህም አቶ ሳሙኤል ዲነጋን አናገርን፡፡ የመድኃኒአለም አጠቃላይ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው፡፡ ተማሪዎቻቸውን በዘንድሮው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ማለፊያ ፈተና መልካም ውጤት እንዲያገኙ ደፋ ቀና እያልን ነው አሉን። ከክፍል ውጪ በሚሰሩ ልምምዶችም ጭምር መግቢያ መውጫ ማሳጣታቸውን ይናገራሉ፡፡ በትምህርት የላቁ ተማሪዎች ታናናሾችን የማገዝ ተግባርም እየከወኑ እንደሚገኙ ገለጹ፡፡

የመዲናይቱ ትምህርት ቢሮም ለተማሪዎች ፈተና ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን አቶ ሳሙኤል ይገልጻሉ። እሳቸውና ትምህርት ቤታቸውም ከሞላ ጎደል በቂ ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ጠቆሙ፡፡ ለፈተና ዝግጅቱ ወገባችንን አጥብቀናል አሉ፡፡ ያሳለፍነው ዓመት ተፈታኞች ከባድ ወቅት በአቶ ሳሙኤል ተወስቷል፡፡ በኮቪድ ምክንያት ዘጠነኛ ክፍልን ሳይማሩ ያሳለፉ ልጆች ይገኙ እንደነበርም ጭምር፡፡

አቶ ሳሙኤል የተማሪዎቻቸው ውጤት ከዓምና እንዲሻል እየሰሩ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በእነ አቶ ሳሙኤል ትምህርት ቤት ውስጥ እስከ ሀምሌ አምስት ድረስ የክለሳ ስራ ይሰራል፡፡ በዚህ ዓመት ስምንት መቶ አካባቢ ተማሪዎች ይፈተናሉ፡፡ 745 በመደበኛና 51 ያህሉ ደግሞ በማታ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ናቸው። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎቹን ለማብቃት የልጆቹን ክፍተት በመሙላት ላይ ነው፡፡ ከወላጆች ጋርም ጭምር በመነጋገር ለልጆቹ አዳዲስ የማጥኛ ሥርዓቶችን ቀይሷል፡፡

ቀጣይ ጉዟችንን ወደ ራዲካል አካዳሚ ትምህርት ቤቶች አድርገናል፡፡ አዜብ ብርሃነን አነጋግረናል። የትምህርትቤቶቹ ጄነራል ማኔጂንግ ዳይሬክተር ናቸው። ትምህርት ቤታቸው ብሄራዊ ፈተናውን የሚመጥን ዝግጅት እያደረገ ነው ብለዋል፡፡ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ተግባር ተኮር ትምህርት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ በየወቅቱ ተማሪዎቻቸውን ቁመና የሚመዝኑበት አሰራር መዘርጋታቸውንም ይገልፃሉ። ተማሪዎች የራሳቸውን የአጠናን ዘዴ የሚያዳብሩበት መድረክ ማመቻቸታቸውንም በማከል፡፡

ተቋሙ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን በቤትም እንዲያጠኑ ያደርጋል፡፡ በትምህርትም በሥነልቦናም እንዲበረቱ ጥረት ያደርጋል፡፡ በቤት እንዳይዘናጉ ያግዛል፡፡ ኦንላይን ትምህርት ይሰጣል። ከኦላይን ትምህርት ውጤታቸውን በመመልከት ምላሽም ይሰጣል፡፡

ዳይሬክተሯ ትምህርት ቤታቸው ባሳለፍነው ዓመት ከሰማንያ በመቶ በላይ ተማሪዎቹን ማሳለፍ መቻሉንም አውስተዋል፡፡ ከመምህር በተጨማሪ ተማሪ ራሱን በራሱ እንዲያስተምር እድል ይሰጣል ብለዋል፡፡

መምህር ካሱ ኩምሳ ቀጣይ አስተያየት ሰጪ ናቸው። የደጃዝማች ወንድይራድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው፡፡

ተቋሙ ልጆቻቸውን ውጤታማ የሚያደርጉ ዝግጅቶችን በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል። በየሳምንቱ ቅዳሜ ለተማሪዎች ትምህርትና የጥናት መርሀግብ አመቻችቷል፡፡ በፈተናው የሚመጡ የትምህርት አይነቶችን ብቻ ያስጠናሉ፡፡ ለፈተና በተቃረቡ ቁጥር አጫጭር ግንዛቤ ማስጨበጫ ይሰጣል።

ትምህርት ቤታቸው በየዓመቱ በመልካም ውጤት እንደሚታወቅ ገልጸዋል፡፡ ባሳለፍነው ዓመት ከመዲናዋ ያለፉ ተማሪዎች ቁጥር 15 በመቶው የትምህርት ቤታቸው መሆኑንም አውስተዋል፡፡

## “አማራ እና ትግራይ ሁለት ስም ያለው አንድ ህዝብ ነው”

### - አቶ ጊደና መድሕን

የትንሳኤ 70 እንደርታ ፓርቲ አስተባባሪ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ እና የአማራ ህዝብ ሁለት ስም ያለው አንድ ህዝብ ነው ሲሉ የትንሳኤ 70 እንደርታ ፓርቲ መስራችና አስተባባሪ አቶ ጊደና መድሕን ተናገሩ።

አቶ ጊደና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የትግራይ ክልል ጊዜያዊ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጌታቸው ረዳ በአማራ ክልል ተገኝተው ከርዕሰ መስተዳድሩ ዶክተር ይልቃል ከፋለ ጋር የተጀመረውን የሰላም መንገድ ለማፅናት ውይይት ማድረጋቸው ለሁለቱ ክልል ህዝቦች ዘላቂ ሰላም ትልቅ እመርታ ነው፡፡

የሁለቱ መሪዎች ውይይት በሁለቱም ክልሎች መልካም የሰላም ግንኙነት ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው ያሉት አቶ ጊደና፤ የትግራይ እና የአማራ ህዝብ ሁለት ስም ያለው አንድ ህዝብ በመሆኑ ውይይቱ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሁም ለምስራቅ አፍሪካ ቀጣናዊ የሰላም ትስስር ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው ብለዋል፡፡



አቶ ጊደና አክለውም የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንት ጌታቸው ረዳ ባህርዳር ተገኝተው ከዶክተር ይልቃል ጋር ያደረጉት የሰላም ውይይት አስፈላጊ ወደ ሆነው የሰላም ጉዳይ በቀጥታ ለመግባት ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ እንደ አንድ ፖለቲከኛ እጅግ አስደስቶኛል ብለዋል፡፡

በሁለቱም ርእሳነ መስተዳድሮች የተጀመረው የሰላም ግንኙነት እንደ ተጨማሪ ሰላም የማፅኛ መንገድ የሚታይ ነው ብለውም፤ ሰላሙ ቀጥታ ወደ ህዝብ እንዲወርድና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡ ሁለቱም ህዝብ በሃይማኖት በባህል እንዲሁም ለአገር ፖለቲካ በከፈሉት መስዋእትነት አንድ ህዝብ ናቸው ሲሉም አክለዋል፡፡

ሁለቱም ህዝብ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም በማህበራዊ ጉዳይ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ጋር በሰላም እና በነፃነት እንዲኖሩ ከላይ እስከ ታች የሚገኙ መሪዎች ሁል ጊዜ ንግግራቸው ሰላማዊ እና አንድነትን የሚያጠናክር መሆን አለበት ያሉት አቶ ጊደና፤ ይህ ከሆነ እየታየ ያለውን የሰላም መንገድ ለማፅናት ትልቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ትግራይ ክልል ላይ የቆየው ምቹ ያልሆነ የፖለቲካ ምህዳር ሊስተካከል ይገባል ብለውም፤ ክልሉ ማንኛውም ሕጋዊ ዜጋ ገብቶ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ሃሳቡን የሚያንሸራሽርበትና ለህዝቡ የሚጠቅም ጉዳይ እንዲስተናገድ ጊዚያዊ መስተዳድሩ ኃላፊነቱን እንዲወጣም አሳስበዋል፡፡

## በክልሉ በ150 ሚሊዮን ብር ወጪ የመጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ነው

### - ከ133 ሺህ በላይ መጻሕፍት ለተማሪዎች ተሰራጭቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል 150 ሚሊዮን ብር ተመድቦ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ያደረጉ ከ730 ሺህ በላይ የመማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ እንደሚገኝ የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። ከ133 ሺህ በላይ መጻሕፍት ለተማሪዎች መሰራጨቱ ተገልጿል፡፡


የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አተገባበር በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜም 150 ሚሊዮን ብር ተመድቦ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት መሰረት ያደረገ ከ730 ሺህ በላይ የመማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ነው ፡፡

የአዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ ተግዳሮት እየሆነ ያለው ሥርዓተ ትምርቱን መሰረት ያደረገ የመማሪያ መጻሕፍት ስርጭት በጊዜው ማድረስ አለመቻሉ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች መጻሕፍት ማዘጋጀት የክልሎች ኃላፊነት በመሆኑ የክልሉ መንግሥት ከ186 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች መማሪያ የሚሆን ከ730 ሺህ በላይ መጻሕፍት ለማሳተም ውል እንደገባ ገልጸዋል፡፡

እስካሁን ባለው ጊዜ ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች 133 ሺህ በላይ መጻሕፍት ማከፋፈል መቻሉን አመልክተው፤ ቀሪዎቹ መጻሕፍቶች እስከ ሰኔ መጨረሻ ድረስ ህትመታቸው እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል፡፡

በተያዘው ዓመት በክልል ደረጃ ለሰባተኛና ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ማድረስ እንደተቻለ ተናግረው፤ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በወቅቱ ለማድረስ አዳጋች በመሆኑ በሶፍት ኮፒ ለማድረስ ጥረት እንደተደረገ መሆኑን ነው የጠቆሙት፡፡

እንደ አቶ አብዱ ሀሰን ገለጻ፤ ከዕቅዱ አንጻር የመማሪያ መጻሕፍት ለተማሪዎች በወቅቱ ያልደረሰበት ምክንያት አብዛኞቹ ክልሎች መጻሕፍትን በማሳተም ላይ ናቸው፡፡



አቶ አብዱ ሀሰን

ይህን ተከትሎ እንደ አገር ያሉ ማተሚያ ቤቶች ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ በሚፈገው ጊዜ ማድረስ አልተቻለም። ሌላው የዶላርና የወረቀት እጥረትም ተግዳሮት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ምንም እንኳን ህትመቱ እየተከናወነ ቢሆንም ጊዜው የአገር አቀፍ ብሄራዊ ፈተናዎች ህትመት የሚከናወንበት በመሆኑ ማተሚያ ድርጅቶች የመጻሕፍትን ህትመት በማቋረጥ ወደ እነዚህ ሥራዎች የሚገቡበት ሁኔታ እንዳለ አውስተዋል፡፡

መጻሕፍት ለተማሪዎች በወቅቱ ተደራሽ አለመደረጉ መምህራን የሚሰጥዋቸውን መልመጃዎች ቤታቸው ሄደው እንዳይሰሩና እንዳያነቡ ከባድ ይሆንባቸዋል ነው ያሉት፡፡

የአዲሱ ሥርዓት ትምህርት በአገር በቀል እውቀቶችና ተግባር ተኮር ትምህርቶች ላይ ትኩረት በማድረግ በትምህርት ዘርፉ ላይ እየታየ ያለውን ክፍተት ለመሙላት የራሱን ሚና እንደሚጫወት ነው ያነሱት፡፡

የክልሉ መንግሥት በዘንድሮ ዓመት የታየውን የመማሪያ መጻሕፍት እጥረት በመፍታት በቀጣይ ዓመት ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚያስፈልገውን ያክል መጻሕፍት በየግሉ ለማዳረስ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ትምህርት የሁሉም መሰረት በመሆኑ አገር እንድታድግና እንድትበለጽግ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ በትኩረት በመስራት ተወዳዳሪ ትውልድ ማፍራት ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

# የቀላል ባቡር ትራንስፖርት የመዘግየትና ከልክ በላይ የመጫን ችግር አለበት

- በመዲናዋ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች

## የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት እየሰራን ነው

- የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት ድርጅት

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት እየሰጠ ያለው አገልግሎት ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም የመዝገየትና ከልክ በላይ የመጫን ችግር አለበት ሲሉ ተጠቃሚዎች ገለጹ፡፡ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር አገልግሎት ድርጅት በበኩሉ ችግሩን ለመፍታት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ ተጨማሪ ባቡሮችን ወደስራ ለማስገባት እና አገልግሎቱን ለማቀላጠፍ እየሰራሁ ነው ብሏል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የቦሌ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ገነት ገብረእግዛብሔር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ለማህበረሰቡ እየሰጠ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ጥሩ ነው፤ ነገር ግን የመዘግየት ችግር ይታይበታል፡፡

በትራንስፖርት የክፍያ መጠን፣ ከትራፊክ መጨናነቅና ብዛት ተሳፋሪ ከመያዝ አንፃር ከሌሎች ትራንስፖርቶች የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ዘርፍ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ተቋሙ በቀላል ባቡር የትራንስፖርት አሰጣጡ ላይ የሚታየውን የመዝገየት ችግር ፈቶ ተደራሽነቱን ሊያስፋፋ ይገባል ሲሉም ጠይቀዋል፡፡

የሳሪስ ነዋሪ የሆኑት አቶ ገብሩ ብርሃን በበኩላቸው፤ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት በክፍያም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ከሌላው ትራንስፖርት የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

ረዥም የትራንስፖርት አገልግሎት የሚጠይቁ ሰፈሮችን ሳያቆራርጡ ለመጓዝ ከሌሎች ትራንስፖርቶች ተመራጭ ነው፤ ቢሆንም የመዝገየትና ከልክ በላይ የመጫን ችግር ይታይበታል ብለዋል፡፡

የቀላል ባቡር ትራንስፖርት የመንገድ መዘጋጋት ስለማያጋጥመው እየሰጠ ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት ቀልጣፋ ነው ስትል የጀሞ ነዋሪ የሆነችው ወይዘሪት መሰረት ፍቅሩም ገልጻለች፡፡

ወይዘሪት መሰረት አክላም ተቋሙ እየሰጠ ያለው አገልግሎት የሚበረታታ ቢሆንም ከመጠን በላይ የመጫንና የመዝግየት ችግር ይታይበታል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጅነር ሙሉቀን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ምላሽ፤ በቀላል ባቡር ትራንስፖርት የሚታዩ ችግሮችን ፈቶ ለማህበረሰቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡



የባቡሮችን ቁጥር ወደ 75 የማድረስና የተለያየ ብልሽት ገጥሟቸው አገልግሎት የማይሰጡ ባቡሮችን አስፈላጊውን ጥገናና የጎማ ቅያሪ በማድረግ ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ የማድረግ ሥራም እየተሰራ መሆኑን ስራ አስኪያጁ አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም በመዲናዋ ያለውን የትራንስፖርት ችግር ለማቃለልና የቀላል ባቡር የትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነቱን ለማስፋፋት ድርጅቱ ከቻይና መንግሥት በድጋፍ መልኩ ሰባት ቀላል ባቡሮችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት እንቅስቃሴ መጀመሩን ጠቁመዋል፡፡

በመዲናዋ የትራንስፖርት እጥረት በመኖሩ ምክንያት አለመጫንም ሆነ መጫን ችግር ነው ያሉት ሃላፊው ከልክ በላይ የመጫንን ችግርን ለመፍታት የባቡሮችን ቁጥር የመጨመርና የተበላሹ ባቡሮችን የመጠገን ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ኢንጂነር ሙሉቀን አክለውም በኤሌክትሪክ አገልግሎት መቆራረጥ ችግር እየደረሰ ያለውን የትራንስፖርት መቆራረጥና የመዘግየት ችግር ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሰራንበት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ኢንጂነር ሙሉቀን አያይዘውም፤ አገልግሎት ሲሰጡ ከነበሩት 41 ቀላል ባቡሮች መካከል 23 ባቡሮች የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ ሲሆን ቀሪ 18 ባቡሮች ብልሽት ገጥሟቸው አገልግሎት እየሰጡ አይደለም። ባቡሮቹ ከአራት ወር እስከ ስድስት ወር ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ሙሉ ለሙሉ ወደ አገልግሎታቸው እንደሚመለሱ አመላክተዋል፡፡

ቀላል የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎትን ቀልጣፋ ለማድረግ የሚሰራውን ሥራ ማህበረሰቡ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግና በመሰረተ ልማቶች ላይ የሚደርሰውን የተለያየ ጉዳት በመከላከል የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ከእንስሳት ሀብት የሚገኘውን ምርት በሳይንሳዊ ዘዴ ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የእንስሳት ተዋጽዖ አቅርቦትን ለማሳደግ በዝርያ ማሻሻል፣ በመኖ አቅርቦት እና በእንስሳት ጤና ጥበቃ ዙሪያ ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴዎች ተግባራዊ እየተደረጉ እንደሆነ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ተዋጽዖ አቅርቦትን ለማሳደግ እና በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዙሪያ የሚስተዋሉትን ችግሮች ለመፍታት ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴዎች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው።

አገሪቱ ከሌሎች አገራት በተለየ በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ እምቅ ሀብት እንዳላት ገልጸው ይህንን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ብለዋል። ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ሳይንሳዊ ግብርናን መጠቀም ተገቢ እንደሆነና ይህም በእንስሳት ተዋጽዖ አቅርቦት ውጤት እንዲገኝ ያደርጋል ብለዋል።

የዝርያ፣ የመኖ እና የእንስሳት ጤና አጠባበቅ ዘዴዎችን በመቀየር እና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ዘዴን በመከተል ከእንስሳት ሀብት የሚገኘውን ምርት መጨመር ይቻላል ያሉት ዶክተር ፍቅሩ፤ ይህንን ለማሳካት ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት ጋር በቅንጅት ለመስራት አቅጣጫዎች እንደተቀመጡ ገልጸዋል።

ባለፉት ጊዜያት በመኖ ሀብት ላይ በተሰራው የዝርያ ማሻሻያዎች አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል። ይሁን እንጂ እንደአገር አሁንም በመኖ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ እጥረት አለ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከተለመደው አሰራር ለመውጣት በክልሎች የመኖ ሀብት ስትራቴጂን በማውረድ ለአርሶ አደሮች የመኖ ሀብት ማሻሻያ



ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ

ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በቀጣይም አርሶ አደሩ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት እንዲችል ይደረጋል ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፤ በተለይ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ እንስሳት የሚገኘው የወተት ምርት አቅርቦት በቂ ባለመሆኑ የዝርያ ማሻሻያ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል። ለዚህ ውጤታማነት የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላትን የማጠናከር እና ያላቸውን አቅም አሟጠው እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ እየተሰራ ነው።

በአሁኑ ወቅት የከብቶች ዝርያን የማሻሻል ሥራ ወጥ በሆነ መንገድ አለመተግበሩ በዘርፉ ትልቅ ተግዳሮት መሆኑን ጠቅሰው፤ ለወተት ምርታማነት መጨመር በቂ የመኖ አቅርቦት መኖር ወሳኝ በመሆኑ ከዚህ አኳያ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት አቅጣጫ ተቀምጧል። መንግሥት ከሚያቀርበው የተሻሻለ መኖ በተጓዳኝ የግል ዘርፉ በስፋት ሊሰማራበት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትም ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነ አንስተዋል።

ገበያው ላይ ለዋጋ መጨመር አንዱ ምክንያት የመኖ አቅርቦት እጥረት እንደሆነ አንስተው፤ እንደ በቆሎና አልፋ የተሰኙ መኖዎችን የማምረት ስራ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተዋል።

# በመዲናዋ አምስቱም የመግቢያ በሮች አዳዲስ የገበያ ማዕከላት እየተገነቡ ነው

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የዋጋ ንረት ለማረጋጋት በአምስቱም የከተማዋ መግቢያ በሮች ባሉ አካባቢዎች አዳዲስ የገበያ ማዕከላትን የመገንባትና ነባሩን የማስፋፋት ሥራ እየተሰራ እንደሆነ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማው ላይ ያለውን የዋጋ ንረትና የምርት አቅርቦት እጥረት ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ ቦታዎች የገበያ ማስፋፋት ሥራ በልዩ ትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡ እየተገነቡ የሚገኙት የገበያ ማዕከላት በስፋት የግብርና ምርት በሚገባባቸው አቃቂ፣ ሰበታ፤ አምቦ፣ ሱልልታ እና ጣፎ በሮች አካባቢ ነው፡፡

ምርት የሚገባባቸው በአምስቱ የከተማዋ በሮች ትልልቅ ገበያ ማዕከላት የተገነቡና አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ መሆኑን አመልክተው፤ ተጨማሪ አዳዲስ የገበያ ማዕከላትን የመገንባትና የማስፋፋት ሥራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሚገነቡትና የተገነቡት የገበያ ማእከላት አምራች አርሶ አደሮች ምርቶቻቸውን እንዲያከማቹና በቀጥታ ለሸማች እንዲሸጡ እድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

የካራአሎ የገበያ ማእከል ፣ የአቃቂ የገበያ ማእከልና የኮልፌ ብርጭቆ የግብይት ማዕከል ግንባታቸው ተጠናቀው ለህብረተሰቡ ምርቶችን በስፋትና በተመጣኝ ዋጋ በማቅረብ አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙም ገልጸዋል፡፡

በተጨማም የንፋስ ስልክ ላፍቶ አትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማእከል፣ የጀሞ ሁለገብ የገበያ ማእከል እንዲሁም የአቃቂ የሰብል የገበያ ማእከል ግንባታዎች ቀደም ሲል ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት ሶስት የገበያ ማእከላት እየተገነቡ ይገኛሉ ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የአትክልት፣ ፍራፍሬና የሰብል ምርቶች የሚቀርቡበት የኮልፌ ቀራንዮ



አትክልትና ፍራፍሬ የገበያ ማእከል ግንባታው 60 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በለሚኩራ ክፍለከተማ ሁለት ማእከላት እያንዳንዳቸው ግንባታቸው አፈጻጸም 60 እና 19 በመቶ እንደሚገኝ አስታውቀው፤ የሁሉንም ግንባታ በዚህ በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ እየተሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በላፍቶ የገበያ ማእከል የማስፋፊያ ግንባታ 78 በመቶ የደረሰ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ ዓመት ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው፡፡ የማእከላቱን ተደራሽነት ለማሳደግም በየአካባቢው የገበያ መሰረተ ልማትን ማስፋፋት የሚያስፈልግ በመሆኑ ቢሮው ከግል ባለሀብቶች ጋር በጋራ ለመስራት አቅዶ እየሰራ ነው ሲሉ አቶ መስፍን ገልጸዋል፡፡

የገበያ ማዕከላቱ አርሶ አደሩ በሕገወጥ ደላላና ነጋዴ ይበዘበዝ የነበረበትን ሁኔታ በመቅረፍ ምርቱን በተገቢው ዋጋ ሸጦ ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም ለሸማቹ ህብረተሰብ የምርት አቅርቦትን በመጨመርና የግብይት ሰንሰለትን በመቀነስ የዋጋ ንረትና የምርት ዕጥረትን ይፈታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የገበያ ማእከላት ለሸማች ማህበረሰብ ምርቶችን በአቅራቢው በተመጣጣይ ዋጋ ከማቅረብ ባለፈ በከተማ ደረጃ ያለውን ሕገወጥ ንግድ፣ የምርት አቅርቦትና ጥራት ችግር በመቅረፍ፣ የኑሮ ውድነቱን ጫና በመቀነስ እንዲሁም የገበያ መረጋጋት በመፍጠር እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ይፈታሉ ተብሎ እንደሚታመን ተናግረዋል፡፡

ዜና

# በክልሉ ከ5 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ላይ እንሰት እየለማ ነው

**አምሳሉ ፈለቀ**



አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ለእንሰት ሀብት ልማት ትኩረት በመስጠትና በስፋት በማምረት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ መምሩ ሞኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ለምግብነት ከሚመረቱ ሥራስር ሰብሎች አንዱ እንሰት ሲሆን ከሌሎች ሰብሎች ባልተናነሰ የእንሰት ሀብትን ምርታማነት በማሳደግ ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡

በአካባቢው ባለፉት የተለያዩ ጊዜያት የተከሰቱ የአየር ንብረት ተጽዕኖዎችን ታሳቢ በማድረግ ሰብሎች በድርቅ ሲጠቁ እና ምርታማነታቸውም በዚያው ልክ ሲጎዳ አይተናል ያሉት ኃላፊው፤ እንሰት በባህሪይው የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል በመሆኑ በስፋት እንዲለማ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ይህም ከአየር ንብረት ተጽዕኖ አንጻር ሰብሎች ላይ ጉዳት ሲከሰት የሚፈጠረውን የምግብ እጥረትን ለመቋቋም የሚያስችለው ሰብል በዋናነት እንሰት በመሆኑ በዚህ ምርታማነትን ለማሳደግና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

የተሻሻሉ የእንሰት ዝርያዎችን ከምርምር ማዕከላት በማስመጣት በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት እንዲሁም በሞዴል አርሶአደር ማሳ በማባዛት ለአርሶ አደሮች እንዲሰራጩ እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በሌላ መልኩ በአካባቢው ያሉ ነባር የሆኑ የእንሰት ዝርያዎችን መጠበቅና ምርታማነታቸውን በማሳደግ የአየር ንብረት ተጽዕኖ ወዳለባቸው አካባቢዎች የማሰራጨት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በዚህ መነሻም በክልሉ በዋናነት እንሰት አምራች ከሆኑ ወረዳዎች አምስት ወረዳዎችን በመለየትና የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመሰብሰብ እንዲተከል ተደርጓልም ነው ያሉት ኃላፊው፡፡

በክልሉ በ5 ሺህ 90 ሄክታር መሬት ላይ የተሻሻሉ የእንሰት ዝርያዎችን በስፋት የማልማት ሥራ እየተከናወነ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ መምሩ፤ ከምግብ ሰብል አንጻር ልዩ ትኩረት የተሰጠበት መስክ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ ዋነኛው ትኩረት የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በተያዘው የምርት ዘመን 5 ሺህ የእንሰት ዝርያዎችን ከአረካ ግብርና ምርምር ማዕከል በማስመጣት በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት የማባዛት ሥራ እየተከናወነ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

በክልሉ ለምግብነት አገልግሎት ባሻገር ለመድሃኒትነት አገልግሎት የሚውሉ 34 ዓይነት ነባር የሆኑ የእንሰት ዝርያዎች እንደሚገኙም ይነገራል፡፡

እንሰት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት የሚገኝ ትልቅ ሀብት ሲሆን፤ ከ20 ሚሊዮን በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን ሦስት ጊዜ መመገብ የሚያስችል የሥራስር ሰብል እንደሆነም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## ዘላቂ ሰላምን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፖለቲካዊ ቀውስ እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አብራርተዋል፡፡

በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነትና የጽንፈኝነት አስተሳሰብ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዳይኖር፣ ለበርካታ ሰዎች መፈናቀል፣ ለንብረት መውደምና ለሰው ሕይወት መጥፋት ምክንያት መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት፣ በመነጋገርና በመቻቻል የሚያምን ትውልድ ማፍራት ከተቻለ፤ ጽንፈኝነትን በማስወገድ እና ሰላማዊ አገርን በመፍጠር ለአገር እድገት ያለውን ዕድል ማስፋት ይቻላል ብለዋል፡፡

ይህንን በመረዳት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኑትን ተግባር በኃላፊነት በመስራት በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን በማድረግ ለአገር እድገትና ለማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ አብን ምክትል ሊቀመንበር አቶ መልካሙ ሹምየ በበኩላቸው፤ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ሁሉም ፖለቲከኞች ፖለቲካቸውን በኃላፊነት፣ በሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማራመድ አለባቸው ብለዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት የሚሰማቸው መሆን አለባቸው የሚሉት አቶ መልካሙ፤ ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ፍላጎታቸውን ለማራመድ መንቀሳቀስ አለባቸው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

እንደ አቶ መልካሙ ገለጻ፣ ፖለቲካ የሚያራምዱ አካላት በኃላፊነት ካልሠሩ አገር ላይ የሚያስከትለው ጫና ከፍተኛ ነው፡፡ በአገሪቱ ሰላም እንዳይሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እድገት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

ፖለቲከኞች፣ ማህበረሰቡና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች በቃልና በተግባር ከሚገለጹ የጥላቻ ድርጊቶች በመቆጠብ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን እንደሚገባቸውም አስገንዝበዋል፡፡

## 2 ነጥብ 8 በመቶ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ችግኝ በመትከል የተቀመጠውን ግብ ማሳካት እንደተቻለ ተናግረዋል፡፡

በባለፈው ምዕራፍ ያሳካነው ስኬት እንደምንችል ትጥቅና ስንቅ የሚሆን ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ 50 ሚሊየን ችግኞች በከተማ ደረጃ ለመትከል መታቀዱን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፣ የሚተከሉት ችግኞች ዓለምን በከፍተኛ ደረጃ እያስጨነቀ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ለማስቀረትና በከተማው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ያግዛል፡፡

ምንም እንኳን የከተማዋን የደን ሽፋን በአጭር ጊዜ 15 በመቶ ማሳደግ ቢቻልም ዓለም አቀፍ ከተሞች ከሚጠይቁት መስፈርት በግማሽ ላይ እንገኛለን ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ የሚፈለገውን መስፈርት ለማሟላት ተጨማሪ ሥራ መስራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች፣ መትከል ብቻ ሳይሆን ተንከባክቦ በፍሬው ተጠቃሚ መሆን ያስፈልጋል ፤ ሁሉም የአረንጓዴ ዐሻራውን ቢያኖር በአጭር ጊዜ ከግብ መድረስ ይቻላል ብለዋል፡፡

ከንቲባዋ አክለውም የሃይማኖት ተቋማት ካላቸው ሰፊ ቦታ አኳያ ግንባር ቀደም በመሆን ችግኞች እንዲያስተክሉ ለሃይማኖት አባቶች ጥሪ አድርገዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶክተር) በበኩላቸው አገራት የሚያደርጉት ልማት ዘላቂ ከሚሆኑባቸው ዐቢይ ጉዳዮች መካከል አካባቢን ያልበከለና ጽዱ አካባቢ መፍጠር አንዱ ተግባር ነው ብለዋል፡፡

የአገሪቱ የደን ሽፋን ከነበረበት ሦስት በመቶ በመነሳት በአገር አቀፍ ደረጃ 17 በመቶ መድረሱን የጠቀሙት ሚኒስትሩ፤ አገሪቷ ከገጠማት ከፍተኛ የደን መመናመን አኳያ እንደ አገር የታቀደውን ከግብ አድርሶ ተጨማሪ ሥራ መስራት ያስፈልጋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር ግርማ ገለጻ፣ ከተሞች አካባቢ ችግኞች ሲተከሉ የከተማ መሠረተ-ልማት በማይጎዱና ከውበት ባሻገር አበቦቻቸው ለጤና ተስማሚ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ መሆን ያስፈልጋል፡፡

በዘንድሮ ክረምት እንደአገር ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል ታቅዷል ያሉ ሲሆን ለዚህም ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞች ተዘጋጅተዋል፡፡

ዶክተር ግርማ አክለውም ችግኞች የሚተከሉበት እስከ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬትና አራት ቢሊዮን የችግኝ መትከያ ጉድጓድ ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

እስከ አሁን ድረስ ግማሽ ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል ያሉት ዶክተር ግርማ፤ ሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ-ግብር 60 በመቶ ጥምር ግብርናና ፍራፍሬዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚሰራ እንደሚሆን አመላክተዋል።

በመርሃ ግብሩ የፌዴራልና የከተማው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አትሌቶች እንዲሁም ከሁሉም ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።

‹‹ነገን ዛሬ እንትከል›› በሚል መሪ ሃሳብ የሁለተኛው ምዕራፍ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ-ግብር በአገር አቀፍ ደረጃ በአፋር ክልል በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) መጀመሩ የሚታወስ ነው፡፡

## ዩኒቨርሲቲዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠንካራ ሥራዎች ተሰርተዋል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ፈተናው በኦንላይን የሚሰጥ በመሆኑ የኔትወርክ ዝርጋታ ተከናውኗል ብለዋል።

ይህም ውጤታማ እንዲሆን የኮምፒተር እና የሌሎች ቁሳቁሶች ግዢ ተፈጽሟል። መጠገን ያለባቸውም ተጠግነዋል ያሉት ዶክተር መገርሳ፤ የመሰረተ ልማት ክፍተት እንዳይኖር እና የተሰሩት ሥራዎችን የመፈተሽ ሥራ መሰራታቸውን አብራርተዋል።

ከዚህም ባለፈ ከዩኒቨርሲቲው አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች እንዳያጋጥሙ እና የሚያጋጥሙ ከሆነም በቶሎ መፍትሄ ለመስጠት ከኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በጋር እየተሰራ እንደሆነ አስገንዝበዋል።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ፕሮግራሞች አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶክተር ተክሉ ገመቹ በበኩላቸው፤ የጅማ ዩኒቨርሲቲ በአራት ካምፓሶች ባሉት በቂ የመፈተኛ ክፍሎች የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በመቀበል የመልቀቂያ ፈተናን ይሰጣል ብለዋል።

የጅማ ዩኒቨርሲቲ በአራት ካምፓሶቹ ከ37 ሺህ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን ወደ 600 በሚጠጉ ክፍሎች መፈተን ይችላል። ዩኒቨርሲቲው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን እና የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናን ለመስጠት ከመቼውም በላይ ዝግጁ እንደሆነ እና ከአምናው ልምድ እንዳገኘም ገልጸዋል።

አሁን ላይ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችን ለመውጫ ፈተና ዝግጁ እያደረገ እንደሆነ ጠቁመው፤ ይህም በታቀደው መሰረት እየተከናወነ መሆኑንና ከሐምሌ ወር ጀምሮ ደግሞ የ12ኛ ክፍል መውጫ ፈተና ለሚወስዱ ተማሪዎች ምቹ ሁኔታን የማከናወን ሥራዎችን እንደሚሠራ አስረድተዋል።

የደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናን በዚህ ዓመት ይሰጣል፤ ለዚህም ትምህርት ነክ እና የመሰረተ ልማት ዝግጅት በከፍተኛ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ደግሞ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የተግባርና የመውጫ ፈተና ዳይሬክተር አቶ አለባቸው ጎሽም ናቸው።

በትምህርቱ ዘርፍ ያለው ዝግጅት ለተማሪዎች እና ለመምህራን የአቅም ግንባታ እና የመውጫ ፈተናን በሚመለከት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተሰርቷል ያሉት አቶ አለባቸው፤ ከዚህም ባለፈ ለተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የማጠናከሪያ ትምህርት ተሰጥቷል ብለዋል።

የዚህንም ውጤታማነት ለመለካት በ51 ትምህርት ክፍሎች ለእያንዳንዱ የትምህርት አይነቶች የብቃት መለኪያ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በዚህም ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ ማወቅ ይቻል ዘንድ የሞዴል ፈተና እንዲወስዱ እና ልምድ እንዲኖራቸው መደረጉን ገልጸዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመጀመሪያ ጊዜ በዩኒቨርሲቲዎች መስጠት የተጀመረው ባለፈው ዓመት ሲሆን በዘንድሮ ዓመት ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና የሚሰጥ ይሆናል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የወርቅ ሀብታችንን ከሕገወጦች የመታደጉ ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥል!

ሀገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሕገ ወጥ የማዕድን ፍለጋ፣ ልማትና ግብይት ሳቢያ ከወርቅ ምርቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ማግኘት አልቻለችም፤ ሕገወጥ ተግባሩ የሀገርንና ማዕድኑ የሚለማባቸውን ክልሎችን ገቢ በእጅጉ እየጎዳ ይገኛል።

ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባት ያለበት የወርቅ መጠን እየቀነሰ ስለመምጣቱ በዚህ ዓመት የሰጠው መረጃ ያመለክታል። ወርቅ በስፋት የሚመረትባቸው ክልሎችም ይህንኑ አረጋግጠዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመንግስት የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በተወያየበት ወቅት የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ የስድስት ወር የወጪ ንግድ ገቢ ትንሽ ቅናሽ ለማሳየቱ የተሰጠው አንድ ምክንያት ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ መጠን እየቀነሰ የመጣበት ሁኔታ ነው።

የችግሩን አሳሳቢነት የተረዳው መንግስት ወርቅና ሌሎች የሀገሪቱ ሀብቶች በኮንትሮባንድ ወደ ውጭ እንዳይወጡ ለመቆጣጠር እንደሚሰራም በወቅቱ አረጋግጧል። በቀጣይም የመከላከያና የፌዴራል ፖሊስ ቀዳሚ ተግባር ኮንትሮባንድን መዋጋት፣ በኮንትሮባንድ የሚመዘበረውን የኢትዮጵያን ሀብት መከላከል እንደሚሆን አስገንዝቦም ነበር።

የማዕድን ዘርፉ በሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የነበረው ድርሻ እየቀነሰ መምጣቱን ተከትሎ እንዲሁም በዘርፉ የሚታዩ ሕገ-ወጥ ድርጊቶች ወደ ብሔራዊ የደኅንነት ሥጋት እንዳይሸጋገሩ ችግሮችን የሚለይና መፍትሄ የሚያስቀምጥ ሀገር አቀፍ ካውንስል ተቋቁሞ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

በተግባራዊ እንቅስቃሴውም ሕገወጦች በቁጥጥር ስር እየዋሉ ይገኛሉ። ባለፈው መጋቢት ወር ከወጣ የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይል መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው፤ የጸና የጉዞ ሰነድ፣ የመግቢያ ቪዛ እንዲሁም የመኖሪያ ፍቃድ ሳይኖራቸው በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በጋምቤላ ክልል ወርቅና የተለያዩ ማዕድናት ፍለጋ ላይ የተሰማሩ 45 የውጭ ሀገር ዜጎችንና ሦስት ኢትዮጵያውያንን ከነ-ኤግዚቢት ተይዘዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የፀና የጉዞ ሰነድ፣ የመግቢያ ቪዛ እንዲሁም የመኖሪያ ፍቃድ ሳይኖራቸው በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወርቅና የተለያዩ ማዕድናት ፍለጋ እንዲሁም የማምረት ስራ ላይ የተሰማሩ 47 የውጭ ሀገር ዜጎች በቁጥጥር ስር ውለዋል። በተጨማሪም ዘጠኝ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማኅበራትና ሰባት ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችም ከእነ-ኤግዚቢቱ በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

ይህ በሕገወጥ የማዕድን በተለይም የወርቅ ማዕድን ፍለጋ፣ ማምረትና ግብይት ውስጥ በተገኙ የውጭ ሀገር ዜጎችና ተባባሪዎቻቸው ኢትዮጵያውያን ላይ የሚወስደው እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በተያዘው ሰኔ ወር መጀመሪያ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሕገ-ወጥ የወርቅ ምርትና ግብይት ተግባር ላይ ተሰማርተው የተገኙ 29 የውጭ ሀገራት ዜጎች እና ሁለት ኢትዮጵያውያን ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት መረጃ አመልክቷል። በዚህ ሕገ-ወጥ ድርጊት ውስጥ በባህላዊ መንገድ ወርቅ እንዲያመርቱ ፈቃድ የተሰጣቸው ማኅበራት አመራሮች፣ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገኙ የጥቅም ተጋሪዎቻቸውም ተሰማርተው ተገኝተዋል።

በወርቅ ማዕድን ላይ የሚታየውን ሕገወጥነት ለመግታት ርምጃ መውሰድ ከተጀመረ ወዲህ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እንደጨመረም በቅርቡ የወጣው የጋራ ግብረ ኃይሉ መግለጫ አመልክቷል። መንግስት ሕገወጦቹን በቁጥጥር ስር እያዋለ ያለበት እንዲሁም ይህን ተከትሎም ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠን እየጨመረ ያለበት ሁኔታ ሕገወጦቹን የመቆጣጠሩ ሥራ ውጤታማ እየሆነ መምጣቱን ያመለክታል።

ይሁንና በቁጥጥር ስር ከዋሉት በሕገወጥ ድርጊቱ የተሰማሩ የውጭ ዜጎች፣ የባህላዊ ወርቅ አምራች ማኅበራት አመራሮችና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ካሉ ተባባሪዎቻቸው አኳያ ሲታይ የመከላከልና መቆጣጠር ሥራው በእጅጉ ፈታኝ መሆኑን ያመለክታል። ይህም የበለጠ ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል።

ሕገወጦችን በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ብሔራዊ ባንክ በሚገባው የወርቅ መጠን ላይ ለውጥ ማምጣት የተቻለው የተከናወነውን ጠንካራ ስራ ተከትሎ ነው። ሕገወጥ ድርጊቱን ለመከላከል ብዙ ዝግጅት ተደርጎ፣ ጥናት ተሰርቶ ነው ወደ ስራው የተገባው። በቀጣይም ከዚህ በላይ መስራትን እንደሚፈልግ በሕገወጥ ድርጊቱ ከተሳተፉበት አካላት ማንነት መረዳት ይቻላል።

ሕገወጥ ተግባሩን በመከላከልና መቆጣጠር ስራ የተሰማሩ አካላት ርብርብ ምስጋና ሊቸረው ይገባል፤ ይህን ምስጋና ማቅረብ የበለጠ ኃላፊነትም መስጠት ይሆናልና።

ሕገ-ወጥ ተግባሩ ገቢን የሚያሳጣ ብቻ አይደለም፤ የሀገር ደኅንነት ስጋትም ጭምር ነው እንጂ። ይህም የመከላከልና መቆጣጠር ሥራውም ሰፊና የተጠናከረ መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል። ችግሩን የመፍታቱ ሥራ ከእስከ አሁኑም በላይ የሁሉንም አካላትና የመላውን ሕዝብ ርብርብ በእጅጉ ይጠይቃል።

የእስከ አሁኑ ሥራን የአጠቃላይ ሕገ-ወጥ ንግድ መከላከል ሥራው መጀመሪያ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። እስከ አሁን ባለው መረጃ መሰረት በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በሕገ-ወጦቹ ላይ ርምጃ እየተወሰደ ነው። ይህ ስራ በሌሎች ወርቅ አምራች አካባቢዎች እንደሚቀጥል ይጠበቃል። ይህን የሚመጥን ስራ ለመሥራትም ዝግጁ መሆን ይገባል፡፡

በሕገወጦቹ ላይ የሚወሰደው ርምጃ ፈጣን፣ አስተማሪና የማያዳግም ሊሆን ይገባል። በሌላ አነጋገር ሌሎች ትምህርት የሚወስዱበት ጠንካራ ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፤ ያንን ማድረግ ከተቻለ የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ይቻላል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የትምህርት ሥርዓቱን ከሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ስመታደግ

ትንሳኤ አበራ

በኢትዮጵያ ባህልና ወግ መሠረት ነውር ናቸው ተብለው ትውልዱ እንዳይፈጽማቸው ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡት በርካታ ጉዳዮች ነበሩ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ሌብነት የሚለው ቃል ነውርና አስጸያፊ ድርጊት እንደሆነ ሲነገረን የኖረ ነው። በማህበረሰቡ ባህል ነውር(አጸያፊ) የሆነው ይህ ድርጊት በሃይማኖታዊ አስተምሮትም እንዲሁ የማይደገፍና የማይበረታታ ነው።

በባህልና በእምነት በአንድ ላይ የሚወገዝ በመሆኑ ደግሞ ህብረተሰቡም ወደዚህ መጥፎ ድርጊት እንዳይገባ ያደርገዋል። ይህንን ተላልፎም ተግባሩን ሲፈጸም የተገኘ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። በዚህ መንገድ እየተጓዘ ትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚገኘው በጎ ልምድ ሆኖ ረዘም ላሉ ጊዜያት ቆይቷል።

አሁን ላይ የማህበረሰቡ ባህልና ወግ እየተሸረሸረ ነውር( አጸያፊ) ተብለው ሲወገዙ የኖሩት ተግባራት በተቃራኒ መንገድ በጎ ተግባራት እንደሆኑ እየተቆጠሩ ያለበት ሁኔታ ይስተዋላል። ቀደም ባሉት ጊዜያት ነውር በሚለው የሚታወቁት አጸያፊ ተግባራት አሁን ላይ ጸያፊነታቸው ቀርቶ እንደ መልካም ሥራ በበርካቶቻችን ዘንድ እየተፈጸሙና እየተለመዱ መጥተዋል።

አሁን ላይ በተለይ በገሃድ እየተሰሙና እየታዩ እንዲሁም እየተለመዱ ያሉት የሌብነት ድርጊቶች ትንሽ ብለን ከምንላቸው ቦታዎች ጀምሮ እስከ ትልቅ ብለን እስካስቀመጥናቸው ድረስ በሁሉም ቦታዎች ላይ በሚታወቅ እና በሚታይ መልኩ እየተፈጸሙ እንደሆነ በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህ መጥፎና ሊለመድ የማይገባው አካሄድ አንድ ነገር አስታወሰኝ፤ ‹‹እማዬ ምነው በእንቁላሉ ጊዜ ...›› አለ ሌባው የሚለውን የሌባው ሲቀጣ ያሰማውን ተማጽኖ።

እንደ ማህበረሰብ አሁን ምን ላይ ነን? ወዴትስ እየሄድን ነው? ብለን መጠየቅ የሚያስፈልግ ጊዜ ላይ ያለን ይመስለኛል። ሌብነት አሁን ባለው አያያዙ ቀጥሎ ስር ከሰደደ በቀላሉ የምንፈታው ጉዳይ አይሆንም። ሌብነት ለመከላከል እየተሰራ ባለው ሥራ የመጀመሪያ ሊሆን የሚገባው ሌብነትን የሚጠየፍ ትውልድ ማፍራት ላይ ማተኮር እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ሲመክሩ ይሰማል።

ሌብነትን የሚጠየፍ ትውልድ ለማፍራት ደግሞ ከሁሉም በላይ ትውልድ የሚያፈሩ ተቋማት ጥልቁን ኃላፊነት ሊወስዱ ይገባል። ለዛሬም ላነሳ የፈለኩት በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፤ በተለይም ሀሰተኛ የትምህርት መረጃን በሚሸጡ ተቋማት ዙሪያ አሁን አሁን መማር ሳይስፈልጋቸው፣ እውቀት የሚለው ነገር ሳያሳስባቸው፤ ብዙም ሳይለፉና ሳይደክሙ እቤታቸው ቁጭ ብለው የፈለጉት አይነት የትምህርት ማስረጃ በቀላሉ መግዛት የሚችሉ ዜጎች ቁጥር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። እነዚህ ሕገወጦች በየሥራ መስኮቹ ተሰግስገው ስራዎች በአግባቡ በሚመጥናቸው ባለሙያዎች እንዳይሰሩ ተግዳሮት እየሆነ ነው።

ሰው እውቀትና ችሎታን ሳይኖረው እውቀት በብሩ መግዛት ከቻለ፤ በአቋራጭ መንገድ የሚፈልገው ኃላፊነት ሆነ ሙያ ላይ መቀመጥ ከቻለ ሁሉም ነገር እዚያ ጋር ነው የሚያበቃው። ሳይለፋና ሳይደክም እውቀት ሳይፈልግ ያለምንም ችሎታ በቦታው ላይ መቀመጥ ከቻለና ኃላፊነት ከተሰጠው በሚፈልገውና በሚመስለው ጎዳና እንደ ውሃ የሚፈስ ከሆነ አካሄዱ ሀገርና ሕዝብን ችግር ውስጥ መክተቱ የማይቀር ነው።

በሀገራችን የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እየተስፋፋ በመምጣቱ ምክንያት በርካቶች በሀሰተኛ ትምህርት መረጃ የማይመጥናቸው ቦታና ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል። በየክልሉ በተለያዩ ዞንና ወረዳዎች ሳይቀረ የትምህርት ማስረጃ ማጣራት በሚያደርጉበት ጊዜ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሠራተኞች የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እንደተገኘባቸው ስለመሆኑም በስፋት እየተነገረ ነው።

በኛ ሀገር ሀሰተኛ የትምህርት መረጃን በሚሰጡና በሚያቀርቡ አካላት ላይ የሚወሰደው እርምጃ እምብዛም ነው። አስተማሪ እርምጃ ተወስዶ ለሕዝቡ ሲነገርም አይሰማም። የሚመለከታቸው አካላት በችግሩ ዙሪያ የማያዳግም እርምጃ ቢወሰድ ኖሮ ዛሬ ላይ በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ እንዲህ አቅላቸውን እስከምንስት ድረስ ውስጡ ገብተን ባልተቦራጨቅን ነበር።

> **ሰው እውቀትና ችሎታን ሳይኖረው እውቀት በብሩ መግዛት ከቻለ፤ በአቋራጭ መንገድ የሚፈልገው ኃላፊነት ሆነ ሙያ ላይ መቀመጥ ከቻለ ሁሉም ነገር እዚያ ጋር ነው የሚያበቃው**

ባለፈው ወር የትምህርት ስልጠና ባለስልጣን እንዳስታወቀው የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ ከተደረገባቸው ከአምስት እስከ ስድስት በመቶ ትክክለኛ አለመሆናቸው አረጋግጧል። በእነዚህ ተቋማት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የመረጃ ማደራጀት ስራዎችን እየሰራ መሆኑን አስታውቋል። ከአምስት እስከ ስድስት መቶ የሚሆኑት የሚለው ቁጥር በራሱ ምን ያህል ችግሩ ውስጥ እንዳለን ማሳያ ነው። ችግሩ ምን ያህል የገነገነ እንደሆነ ያመላክታል።

በቅርቡ የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ የሚፈልጉ ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ በመሆን የማረጋገጫ ወረቀት ማግኘት የሚችሉበት ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ማስታወቁን ይታወሳል። ይህ እሰየው ይበል የሚያሰኝ ተግባር ነው።

ቴክኖሎጂን መጠቀም ሙሉ ለሙሉ ሀሰተኛ የትምህርት መረጃ አሰጣጥን እስከ ወዲያኛው ለማጥፋት ባያስችል እንኳን ሥርዓት ለማስያዝ የሚያግዝ ነውና ለተግባራዊነት መፍጠንን ይጠይቃል። ያለንን የቴክኖሎጂ አቅም አሟጦ በመጠቀም የሌብነትን ሰንሰለት በመበጣጠስ ሌብነት የሚጠየፍ ትውልድ ለማፍራት ግን ከዛሬ ጀምሮ ባለን አቅም ልንቀሳቀስ ይገባል ።

በተለይ በዚህ የተበላሸ አሠራር ውስጥ ተዘፍቀው የሚገኙ አካላት ዞር ብለው እራሳቸው መፈተሸ አለባቸው። አስነዋሪ ተግባራቸው በሀገርና በትውልድ ላይ የሚፈጸም ታሪክ ይቅር የማይለው ወንጀል ነውና ከድርጊታቸው ተቆጠበው የመፍትሔው አካል መሆን አለባቸው ባይ ነኝ። የሌብነት ትንሽ ሆነ ትልቅ የለውም፤ ሌባ ያው ሌባ ነው። ሥርዓት ሊበጅለት የግድ ይለዋል፤ በተለይ በሀሰተኛ የትምህርት መረጃ ጉዳይ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል።

ቸር እንሰንብት።

# ፋሽን

## የቲሸርት ማምረቻ ክርን ለአልባሳትና ጫማዎች ማስዋቢያ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በሀገራችን ቀደም ሲል የእጅ ጥበበኛው የሚያበረታታው አልነበረም፤ ኑሮውንም በመገለል ነበር የሚመራው። ይህ ሁኔታ ሙያውን ለማቆየትም ሆነ ለማሳደግ ሳያስችል ኖሯል። ሙያተኛውም በሙያው ተገቢውን ጥቅም ሳያገኝበት ዘመናት አልፈዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ነገሮች ተቀይረዋል። የእጅ ጥበበኛው ወቅቱ ከሚጠይቀው ፋሽን ጋር ለመራመድ ሌተቀን እየተጋ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የእጅ ሥራ ሙያ ክህሎት በትምህርት እንዲታገዝ የማድረጉ ጥረት እየተጠናከረ መጥቷል። የእጅ ጥበብ ሙያተኞች ምርቶች በእጅጉ ተፈላጊ እየሆኑ ናቸው። ባሙያዎችም ሙያቸውን ለማሳደግ ያላቸው ፍላጎትም እየጨመረ ይገኛል።

ባለሙያዎቹ በልምድ የቀሰሙትን እውቀት በትምህርት በመደገፍ የእጅ ሥራ ሙያ እንዲያድግ የራሳቸውን አበርክቶ በማድረግ ላይ ናቸው። በተለያዩ አውደ ርዕዮች፣ ማህበራዊ ሚዲያዎች እና በሌሎች ቦታዎች ላይ የምናያቸው የእጅ ሥራ ውጤቶችን ለዚህ እንደ አንድ ማሳያ ማጠቀስ ይቻላል።

ፋሽን ዲዛይነር ወጣት ነጻነት ተስፋዬ በእጅ ስራ ሙያ ውስጥ ትገኛለች። ፋሽን ዲዛይነር ነጻነት የእጅ ሥራ ሙያን የተማረችው ከእናቷ ነው። በልጅነቷ እናቷ የሚሰሩትን የእጅ ጥበብ እያየች ስላደገች የሙያው ባለቤት ለመሆን አልተቸገረችም። ሙያውን ከልጅነት ጀምሮ እያደገችበት ስለመጣች በፍላጎት ነው የምትሰራው።

‹‹እናቴ የእጅ ሥራዎችን ሠርታ በመሸጥ ነው ያሳደገችኝ›› የምትለው ዲዛይነር ነጻነት፤ ለሙያው ፍቅርና ፍላጎት ያደረባት ያኔ ገና ከልጅነቷ አንስቶም ነው። እናም የእናቷን ሙያ ሊያሳድግላት የሚያስችላትን ትምህርት ለመማር ፍላጎቱ ስላደረባት የፋሽን ዲዛይኒንግ ሙያ ተምራ በምትወደው የእጅ ሥራ ሙያ ላይ ተሰማርታለች።

ዲዛይነሯ እንደምትለው፤ ቀደም ሲል እናቷ በክር ግብዓት ተጠቅመው ሲሰሩት የነበረው የእጅ ስራ ሙያን የተሻለ ደረጃ ለማድረስ ጥረት በማድረግ ላይ ትገኛለች።



ሙያው እንዲያድግ ባላት ፍላጎት ያላትን ክህሎትና በዘርፉ ያገኘችውን እውቀት ተጠቅማ ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ ከዘመኑ ጋር የሚራመዱና የተጠቃሚውን ፍላጎት የሚያሟሉ ዲዛይኖችን በመሥራት የግል ጥረቷን እያደረገች ነው። በአሁኑ ጊዜም በተለያየ ዲዛይን ከምትሰራቸው አልባሳት ቲሸርት ይጠቀሳል። አልባሳቱንም ክር በመጠቀም ነው የምታዘጋጃቸው።

በተጨማሪም በዚሁ በክር ግብዓት በተለያየ ዲዛይን የተዋቡ ጫማዎች፣ ቦርሳዎች፣ ብርድ ልብስ፣ ቀሚሶች፣ መደረቢያዎች፣ ኮፍያዎች በመሥራት ላይ ስትሆን፣ ከሀገር ባህል (የሀበሻ ልብስ) ጋር በመቀላቀል የምትሰራቸው የተለያየ የአልበሳት አይነቶች መኖራቸውንም ዲዛይነር ነጻነት ትገልጻለች።

የሀበሻ ቀሚሶቹን በሚፈለገው ዲዛይን ከሠራች በኋላ በሚፈለገው ቦታ ልክ ጥልፍ እንደሚሰራበት ሁሉ ቲሸርት የሚሰራበትን ክር በመጠቀም የሚፈለገው ዲዛይን በማውጣት እንደምትሰራም ገልጻ፤ ከእጅ ሥራ ሙያው በተጨማሪም የተለያዩ አልበሳት ዲዛይን በማድረግ እንደምትሰራ ትናገራለች።

ዲዛይነር ነፃነት እነዚህ ሥራዎቿን ለገበያ ለማቅረብም የዲጂታል ቴክኖሎጂ ጠቅሟታል። ቴሌግራም፣ ፌስቡክ፣ ኢንስቲግራም እና ቴክ ቶክ የመሳሰሉትን የማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎች አማራጮቿ እንደሆኑ ገልጻለች።

በተጨማሪ ደግሞ በተለያዩ ኤግዚቢሽኖች ላይ በማቅረብ ሥራዎቿን ለማስተዋወቅ ጥረት እያደረገች ነው። በዚህም አሁን ላይ ምርቶቿን የሚፈልጉ ደንበኞች በውጭ ሀገር እንዳሉ ተረድታለች፤ ከሀገር ውስጥ ደንበኞቿ መካከልም ብዙዎቹ ሥራዎቿን ካዩ በኋላ በትእዛዝ እንድታቀርብላቸው ይጠይቋታል።

አልባሳቱን ለመሥራት የምትጠቀምበት የጨርቅ ክር ግብዓት ጥራት በደንበኞቿ እያስመሰገናት መሆኑን ጠቅሳ፣ እስካሁንም ለገበያ ያቀረበቻቸው አልባሳት በጣም ጠንካራና ረጅም ጊዜ ማገልገል የሚችሉ መሆናቸውን ከደንበኞችዋ በምታገኘው ግብረ መልስ አረጋግጣለች።

ዲዘይነሯ እንደምትለው፤ አሁን ላይ ምርቶቿን በተቻለ መጠን ህብረተሰቡን በማይጎዳ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበች ነው። የአንድ ቦርሳ ዋጋ 1ሺ500 እስከ 3ሺ500 ትሸጣለች። ምርቶቹ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝተዋል፤ የህብረተሰቡም ፍላጎቱም በጣም ከፍተኛ ነው፤ ብዙ ትእዛዝም እየተቀበልን ነው፤ ብዙ ደንበኞች ቦርሳዎቹን ከሀገር ባህል አልባሳት ጋር ለመጠቀም ይመርጧቸዋል ትላለች።

ዲዛይነር ነፃነት እንደገለጸችልን፤ አልበሳቱን በተለያየ መልኩ ዲዛይን አድርጎ በብዛት ለማምረት ጊዜ ይወስዳል፤ ሥራውም ያደክማል። በመሆኑም ብዛት ያለው የሰው ኃይል ይፈልጋል። በብዛት የሰው ኃይል ይዞ ለመሥራት የገንዘብ አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ ለጊዜው ከሁለት የቤተሰቧ አባላት ጋር በመሆን ነው ሥራውን እየሰራች የምትገኘው። አቅሙ ቢኖር ግን ዘርፉ ለብዙዎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

‹‹ምርቶቿን ባልተለመደ መልኩ ለየት ባለ ፋሽን ስለምሰራቸው ተጠቃሚዎቹ በዚያው ልክ ይወዷቸዋል። ለተለያዩ ፕሮግራሞች፣ ዝግጅቶች ጨምር ስለሚፈልጓቸውም በትዕዛዝ ያሰራሉ›› የምትለው ዲዛይነሯ፤ በተለይ ፋሽን የሚከተሉ ሰዎች ሥራዎቿን ወደው እንደሚገዟት ትናገራለች።

ዲዛይነሯ እንደምትለው፤ እነዚህን ምርቶች ከሀገር ውስጥ ፍጆታ በተረፈ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ገቢ ማግኘት ይቻላል። ምርቶቹን ለመስሪያ የሚሆኑ ጥሬ እቃ ከውጭ ለማስመጣት የሚጠይቀው ቀረጥ ውድ ስለሆነ በሚመለከተው በኩል በቅናሽ እንዲገባ ቢደረግ በግብዓቱ ላይ እሴት እየጨመሩ ወደ ውጭ መልሶ በመላክ ሀገሪቱን ከዘርፉ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

እሷ እንዳለችው፤ ህብረተሰቡ ምርቶቹን ገዝቶ ለመልበስ በጣም ይፈልጋል፤ አሁን ላይ ያለው አቅርቦትና ፍላጎት ግን አይጣጣምም። ጥሬ እቃ ከውጭ የሚገባበት ዋጋ ከፍተኛ መሆኑ የምርቶቹ ዋጋ በዚያው ልክ ውድ እንዲሆን ያደርገዋል። ጥሬ እቃው በሀገር ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ቢኖር ዋጋውም ይቀንሳል። ህብረተሰቡም የሚፈልገውን ምርት በሚፈልገው ዋጋ ማግኘት ይችላል።

ወጣቷ ለሙያው ክብርና ሙያውም እንዲያድግ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ትናገራለች። ለሙያው እድገትም የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነችም ትገልጻለች። ‹‹ለቲሸርት መስሪያ በሚውለው ክር በተለያየ ዲዛይን የሚሰሩትን እነዚህን አልባሳትን የማምረቱ ሙያ በተወሰኑ ሰዎች እጅ ላይ ብቻ መቅረት የለበትም የምትለው ዲዛይነሯ፣ ሙያውን ለትውልድ ማስተላለፍ እንደሚገባም ነው የምትገልጸው።

በተለይ ወጣቱ ትውልድ ይህንን ሙያ ተምሮ ሥራ ላይ እንዲሰማራ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁማለች። ሙያውን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግም ሆነ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥራ ለመስራት በእሷ በኩል ዝግጁ መሆኗን ትናገራለች። ሙያውን ለሌሎች ማስተላለፍ የምትችልበትን ትምህርት ቤት በመክፈት ለብዙዎች የሥራ እድል ለመፍጠርም ፋሽን ዲዛይነር ነጻነት አስበዋለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ውለታን - በውለታ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አንዳንድ ሰዎች ለሆነ ጉዳይ ምክንያት መፍጠር ሲሹ በዘመንና ጊዜ ያሳብባሉ። ሁሌም እንዲህ ባሰቡ ጊዜ መነሻ መድረሻቸው ያው መከረኛ ጊዜና ዘመን ይሆናል። እነዚህ ሰዎች በየጨዋታቸው መሀል ‹‹አይ ጊዜ ! ›› ማለትን ያበዛሉ። ዘመኑን ኮንነው፣ ጊዜውን ይራገማሉ።

እስካሁን ለሆነውና ወደፊት ለሚሆነው አሉታዊ ድርጊት ሁሉ ተጠያቂ የሚያደርጉት ያለፉበትንና ወደፊት የሚመጣውን አዲስ ዘመንና ጊዜውን ነው። እንደ እኔ ሀሳብ ግን ለክፉ ጉዳዮች ተጠያቂ መሆን የሚገባው ጊዜና ዘመን ሳይሆን ራሱ የጉዳዩ ባለቤት ነው።

በርከት ያሉ ተሳፋሪዎች ከያዘ የሕዝብ አውቶቡስ ውስጥ እገኛለሁ። አጋጣሚ ሆኖ ወንበር አጥተው ከቆሙት መሀል አልተደመርኩም። አስቀድሜ ከያዝኩት መቀመጫ አረፍ እንዳልኩ ከውጭ ወደውስጥ የሚገቡትን ተሳፋሪዎች እየታዘብኩ ነው።

አውቶቡሱ ከሞላ ቢቆይም የያዘው ብቻ የበቃው አይመስልም። ትኬት ቆራጩ አሁንም አንገቱን በመስኮት እንዳሰገገ ነው። እጃቸውን ከዘረጉት ሁሉ ገንዘብ እየተቀበለ ተሳፋሪዎችን ወደ ውስጥ ያሳልፋል። አሁን ሆዱ ያለቅጥ የሞላው አውቶቡስ ሞልቶ ከመፍሰሱ በፊት ‹‹በቃኝ›› ያለ ይመስላል። በሩን እንደምንም ዘግቶ እየተንቀሳቀሰ ነው።

ጥቂት እንደተጓዝን ትንፋሽ ያጣሁ ቢመስለኝ መስኮት ፍለጋ ዓይኖቼን አሻገርኩ። በዚህ አፍታ በጭንቅ ከቆሙት ተሳፋሪዎች መሀል ትኩረቴ በአንድ አዛውንት ላይ አረፈ። ዕድሜ ጠገቡ ሰው ብረቱን እንደምንም ይዘው ይንገዳገዳሉ። ድካም ያዛለው አካላቸው በላብ ወርዝቷል። በቁማቸው ዕንቅልፍ የወሰዳቸው መሰለኝ።

ዞር ብዬ ዙሪያ ገባውን ቃኘሁ። ወንበር ከያዙት አብዛኞቹ ወጣቶችና በጉብዝና ዕድሜ ያሉ ጎልማሶች ናቸው። ደነገጥኩ። ከነዚህ መሀል አንዳቸው እንኳን ስለአዛውንቱ ደንታ ማጣታቸው አሳሰበኝ። አብዛኞቹ ‹‹ባላየ›› በሚባል መልኩ መንገዳቸውን ቀጥለዋል።

‹‹አይ ! ጊዜ ወይ ! ዘመን ማለት አልፈለኩም። እንዴ! ወዴት እየሄድን ነው ? ራሴን ጠየኩት። ደግነቱ ከመልሱ በፊት ሽማግሌው ወንበር ይዘው አየኋቸው። የተባረከች አንዲት ልጅ እግር ቢጤ ተነስታላቸው ኖሯል።

ወዳጆቼ ! ይህን ትዝብታዊ ምሳሌ ማንሳቴ ያለ ምክንያት አልሆነም። እርግጥ ነው በመንገዴ ያጋጠመኝ አይነት እውነት ሁሌም እንደማይሆን አውቃለሁ። አብዛኛው ታላላቁንና ሽማግሌዎችን ያከብራል። ይህ የቆየ ማንነት አሁን ላይ እየሳሳ ቢሄድም ለዘመናት በክብር አብሮን ቆይቷል።

‹‹ነገርን ነገር ያነሳዋል›› እንዲሉ ከዕድሜና አዛውንትነት ጋር ተያይዞ የሚሳስበኝን አንድ እውነታ ልናገር። አሁን ላይ በየቤታችን ብሎም በአካባቢያችን ዕድሜ ጠገብ አዛውንቶች ከጎናችን ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች ዛሬ ላይ ደርሰው ‹‹አረጋውያን›› ሲባሉ እንዲሁ በዋዛ አይደለም። ጥቂት የማይባል የኑሮ ውጣውረድን አልፈው፣ ለሀገርና ትውልድ የሚተርፍ ደማቅ አሻራን አሳርፈው ነው።

እንዲህ አይነቶቹ ታላቅ የሀገር ባለውለታዎች ደግሞ ብድራታቸው ይመለሳል። ሳይሞቱ፣ ሳይረሱ በቁመናቸው በጎነት፣ መልካምነታቸው ይዘከራል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ለትውልድ የሚቀመጠው የታሪክ ቅብብሎሽ አይዛነፍም። ሰንሰለታዊው ጉዞ ሳይዘነፍ በጥንካሬው ይቀጥላል።

አሁን ባለንበት ጊዜ ግን ይህ እውነታ በወጉ ቀጥሏል ለማለት አያስደፍርም። ዛሬ ላይ ወላጆቻቸውን ከመጦር ይልቅ እስከለተሞታቸው በእነሱ አቅምና ትከሻ የሚጦሩ ልጆች በርክተዋል። ተወልደው ያደጉበትን ቤት ከመደጎም፣ እድሜ ያጎበጣቸውን አዛውንቶች ከመደገፍ ይልቅ ለራሳቸው ብቻ የሚያድሩ ልጅ ተብዬ ሽኮሞች በየቤቱ አይጠፉም።

እንዲህ አይነቶቹ ውል አልባዎች መለስ ብለው የወላጆቻቸውን ድካም አይቃኙም። ዛሬም በእነሱ ጥላ አርፈው የእጃቸውን ፍሬ ይጠብቃሉ። የጡረታቸውን ጥቂት ገንዘብ መንጠቅን ይናፍቃሉ። እንደህ አይነቶቹ ልጅ ተብዬዎች ወልደው አሳድገው፣ ቁምነገር ላበቋቸው ወላጆቻቸው ደንታ የላቸውም። ዛሬም ድረስ የእናቶቻቸውን ቁራሽ በፍቅር ሳይሆን በአስገዳጅነት መጉረስ ይሻሉ። ይህ አይነቱን ስሜት ይዘውት ኖረዋልና ‹‹እንጡር ፣ እንደግፍ፣ በዛውም እንመረቅ፣ እንመስገን›› ይሉትን ወግ አይሞክሩትም ።

በሀገረ ቻይና አንድ ልጅ ዕድሜው በደረሰ ጊዜ የወላጆቹን ታላቅ ውለታ እንዲመልስ ይገደዳል። (በእኛም አገር ስንጠቀምበት አይታይም እንጂ በቤተሰብ ሕግ ውስጥ እንዳለ ሰምቻለሁ። ) ወላጆችም ቢሆኑ በልጆቻቸው የሚደረገላቸውን እንክብካቤ ለመቀበል ዝግጁ ናቸው። ይህ በሕግ ተደንግጎ በመመሪያ የጸደቀው ደንብ በየትኛውም ሰበብ ተፈጻሚ ከመሆን የታቀበ አይደለም ።

ወደ እኛ አገር ተጨባጭ እውነታ መለስ ስንል ከመከባበር ባለፈ በዕድሜ የገፉ ወላጆቻችን ብቻ ሳይሆን ላልተወለዱን አዛውንቶች ጭምር እጆቻችንን የምንዘረጋበት አጋጣሚዎች ይኖራሉ።

ይህን ለማድረግ ስንውስን ግን በገሀድ የሚታይ ችግር ስላለና እነሱም ችግሩን መቋቋም ስለተሳናቸው መሆኑ ግልጽ ነው። ወላጆች ዕድሜያቸው በገፋ በደከሙ ጊዜ ለችግር የመጋለጣቸው አጋጣሚ ትኩረት ሰጥቶ የሚረዳቸው ወገን የመጥፋቱ እውነታ ነው። እንዲህ ባይሆንማ እንደውለታቸው ዓይን ጥሎ፣ ጊዜ ወስኖ ‹‹አለሁ›› የሚላቸው ባልጠፋ ነበር።

በሕይወት አጋጣሚ እንደሚታየው ወላጆች አያት በሆኑ ጊዜ ደስታቸው እጥፍ ድርብ ይሆናል። ከልጆቻቸው ይልቅ ለልጅ ልጆቻቸው የሚያሳድሩት ፍቅር በእጅጉ ያይላል። በዚህ መሀል ድካምና ችግር ቢኖር እንኳን ተቋቁመው ያልፉታል እንጂ ፈጽሞ አይከፉም ።

አንዳንዴ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የሕይወት አቅጣጫ ይቀየራል። በሚያርፉ፣ በሚጦሩበት ዕድሜ የልጅ ልጆቻቸውን አሳዳጊዎች ይሆናሉ። ወደዚህ መንገድ የመግባታቸው እውነት ምናልባትም የልጆቹን ወላጆች በሞት ማጣታቸው አልያም በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። እንዲህ መሆኑ ብቻውን ስለነእነሱ አትኩሮት እንዳይኖር ያደርጋል።

በሰለጠኑት ዓለማት የዕድሜ ባለጸጋዎች እንደ ታላቅ ሀብት ይቆጠራሉ። ከእነሱ ጠጋ ያሉም ትርፍ እንጂ ኪሳራ አይገጥማቸውም። እነዚህ አዛውንቶች ልጆች ካላቸው በልጆቻቸው፣ አልያም በቅርብ ዘመዶቻቸው ይደገፋሉ። የአገራቸው መንግስት ፈጽሞ አይተዋቸውም። የዕድሜ ዘመናቸውን አክብሮ የተለየ ቦታ ይቸራቸዋል።

በነዚህ ዓለማት የዕድሜ ባለጸጎቹ በቤታቸው ምቹ ሕይወት ባይኖር እንኳን ለእነሱ ተብሎ በተዘጋጁ ማዕከላት ሙሉ ወጪያቸው ተችሎ ዘላቂ ድጋፍ ይኖራቸዋል። ህክምናን ጨምሮ ውሏቸውን በደስታና ተዝናኖትም ያሳልፉታል።

የእነዚህ አገራት የዕድሜ ባለጸጎች እንደ እኛዎቹ ቀሪ ዘመናቸውን በሀዘንና ትካዜ አይገፉትም። በልዩ ትኩረት፣ የተለየ እንክብካቤና ፍቅር እየተመገቡ ያለፉበትን ዘመን በያዙት ዓለም ደስታ ያጣጥማሉ።

ወደ እኛ ሕይወት መለስ ስንል አብዛኞቹ አንጋፋዎቻችን በዕድሜያቸው ማምሻ ለሀዘንና እንግልት የተጋለጡ ናቸው። ጥቂት የማይባሉትም ያለ ጧሪ ቀባሪ ኑሯቸውን ለመግፋት ይገደዳሉ። ይህ ችግር ከሕዝብ ቁጥር መጨመርና ከኑሮ ማሻቀብ ጋር ለአረጋውያኑ ታላቅ ፈተና ይሆናል። የሀገር ባለውለታነታቸውንም ያስረሳል። ተደጋግሞ እንደሚባለው ‹‹አንድ ትልቅ ሰው ሲሞት አንድ ቤተመጻህፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል›› ብዙ ጊዜ ግን በእጅ የያዙት ወርቅ ሆኖብን ታላላቅ ሀብቶቻችን ስናከብር፣ ዕውቀትና ተሞክሮን ስንጋራ አይስተዋልም።

አረጋውያን የማንነታችን መነሻ፣ የትውልድ መሰረት ናቸው። ‹‹የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ›› እንዲሉ ታላላቆችን በማክበር፣ ውለታቸውን የመመለስ ልምድ ይኑረን። ትናንትን አልፈን፣ ዛሬን ኖረን፣ ነገን ለማየት የእነሱ ታላቅ አሻራ በማንነታችን ስር ታትሟልና።

# ነፃ ሃሳብ

## ሀገራችን የምትፈልገው በሰላም እና በእርቅ የተገነቡ ነገዎችን ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

እንደ አንድ ሀገር ወዳድ ወጣት ለሁላችንም የሚጠቅምና የሚበጅ አንድ ሀገራዊ መፈክር ይዤ መጥቻለሁ። ‹ከጦርነት በፊት ሰላም› የሚል መፈክር። ዓለም በብዙ አይነት አስተሳሰብ ውስጥ ናት። እንደ ሰላም ባሉ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ግን አንድ አይነት አቋም ነው ያላት።

ከትላንት እስከዛሬ በሰላም ጉዳይ ላይ የዓለም አቋም ተቀይሮ አያውቅም። ሰላም በመነጋገር፣ በመመካከር እንዲሁም ደግሞ በውይይት የሚመጣ ነገር እንደሆነ የጋራ አቋም አላት። እንደ መልክና ቁመታችን፣ እንደ ውፍረትና ቅጥነታችን የተለያየ ሀሳቦችን የምናራምድ ነን። እኚህ ሁሉ ሀሳቦቻችን ከሌላው ሀሳብ ጋር የሚታረቁት ደግሞ በምክክርና በውይይት ብቻ ነው።

እንደ ፖለቲከኛ ስናየው ደግሞ ይሄ የሀሳብ ልዩነት ገኖ ሲወጣ እናየዋለን። ገኖ መውጣቱ ብቻ ሳይሆን በሀገርና ሕዝብ ላይ የራሱን ጫና የሚፈጥርም ነው። ሰው እንደ ተፈጥሮው ልዩ ሀሳብ እንዳለው ከተረዳን ሀሳቡን ለማክበር አንቸገርም። ችግር የሆነብን ግን የኔ ሀሳብ ካልሆነ፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚለው እኔነትንና ራስ ወዳድነትን የተሸከመ፣ የሌሎችን ሀሳብ ያላማከለ ሀሳባችን ነው። በዚህም ምክንያት ብዙ ጊዜ ሀሳቦቻችንን ማሸነፍ አቅቶን፣ ለእርቅና ለተግባባቶ ጊዜ አጥተን ብዙ ነገር ሆነናል።

ከጦርነት በፊት ሰላም የሚለው መፈክሬ ዘመኑን የዋጀ ሁላችንም የምናምንበት አዲስ አስተሳሰብ ነው። ጥቂት ስልጡን ሀገራት እየተራመዱበት ያለው እሳቤ ስለመሆኑ አልጠራጠርም። ከጦርነት በፊት ሰላምና ከጦርነት በኋላ ሰላም የተለያዩ ናቸው። እስከዛሬ ከጦርነት በኋላ ሰላምን ስንፈልግ፣ አንድነትን ስንመኝ ኖረናል አሁን ግን ሰላማችንንም ሆነ አንድነታችንን ከጦርነት በፊት መጀመር አለብን።

ከጦርነት በፊት የተጀመረ ሰላምና አንድነት፣ እርቅና ምክክር ሀገርን ያስቀደመ፣ ልማትና ብልጽግናን የተቀበለ ሁሉን ያቀፈ በጎ አስተሳሰብ ነው። ከጦርነት በፊት የተጀመረ ፍቅርና ይቅርታ በማሸነፍ የታጀበ፣ ለሀገር ክብር፣ ለወገን ደጀን የሆነ ነው። ከጦርነት በኋላ ሰላም ግን ከዚህ በተቃራኒ ብዙ ነገራችንን ካሳጣንና ከነጠቀን በኋላ የሚሆን ነው።

እስኪ አስቡት የሰሜኑ ጦርነት በፍቅርና በወንድማማችነት ቀርቶ ቢሆን ኖሮ፣ በመከራ ያለፉት እነዛ ሁለት የጦርነት አመታት በእርቅና በምክክር፣ በውይይትና በስምምነት አልፈው ቢሆን? እስኪ አስቡት እነዛ ሁሉ ሞትና የአካል ጉዳቶች፣ መፈናቀሎችና ጉስቁልናዎች በወንድማማችነት ተሸንፈው ቢሆን? ትርፋችንን..ክብራችንን. አስባችሁታል? ከጦርነት በፊት ሰላም ማለት። ከጦርነት በፊት ፍቅርና ይቅርታ፣ አንድነትና ወንድማማችነት ያልኳችሁ ይሄንን ነው።

እንደ ሀገር እንደ ዜጋ ከምንም በላይ ደግሞ እንደ ፖለቲከኛ ሳንሞትና ሳንጎሳቆል ተነጋግሮ መግባባትን መለማመድ አለብን። በውይይት፣ በንግግር እንዴት ሰላም እንደሚመጣ መማር ይኖርብናል። ትንንሽ ነገሮች ዋጋ ሲያስከፍሉን ሳይ ይከፋኛል። ለኢትዮጵያዊነት የማይመጥን ምናምንቴ ሀሳቦች ለመለያየት ሲዳርጉን ሆድ ይብሰኛል።

ባጣነው ልክ ለማግኘት፣ በከሰርነው ልክ ለማትረፍ ከጦርነት በፊት ወዳለው መንፈስ መመለስ ይኖርብናል። በሰላምና ተግባቦት፣ በእርቅና ምክክር፣ በውይይትና ስምምነት ሀገራችንን ካልታደግናት በምንም አንታደጋትም። ያለፍንበት መንገድ ሊያስተምረን ይገባል። ምን አጥተን ምን እንዳለን፣ ምን ጎሎን ምን እንደሞላን እናስተውል። ተነጋግሮ ከመግባባት፣ ተግባብቶ ሰላም ከመፍጠር በቀር ሁሉም ያለን ሕዝቦች ነን።

እኚህ ብዙ ነገሮች እንዲጠቀሙንና ዋጋ እንዲያወጡልን በሰላምና በፍቅር፣ በአንድነትና በመተቃቀፍ ሊከበቡ ይገባል። ዛሬ ላይ ትንሽ ያላቸው ሀገራት እየበለጡን ነው። እኛ ያለን የሌላቸው፣ ከእኛ በብዙ ያነሰ ነገር ያላቸው ሀገራት እየቀደሙን ነው.. ለምን ካልን እነሱ በሰላምና በመነጋገር ጥቂቱን ነገር አብዝተውታል። እኛ በሰላም እጦት፣ ተነጋግሮ ባለመግባባት ብዙውን ነገራችንን ዋጋ አሳጥተነዋል።

> **እንደ ሀገር እንደ ዜጋ ከምንም በላይ ደግሞ እንደ ፖለቲከኛ ሳንሞትና ሳንጎሳቆል ተነጋግሮ መግባባትን መለማመድ አለብን። በውይይት፣ በንግግር እንዴት ሰላም እንደሚመጣ መማር ይኖርብናል**

ልዩነታችን ይሄ ነው..ሰላም በሌለበት ሁኔታ ውስጥ የሚጠቅም ምንም የለም። ያለን ነገር እንዲጠቅመን ወደ ሰላም እንመለስ። ወደ ሰላም እንይ። ከጦርነት በፊት ወዳለው አዲስ አስተሳሰብ እንማትር።

ከሰሞኑ በኢቢኤስ ቴሌቪዥን ላይ እንግዳ ሆኜ ቀርቤ ነበር። መጽሀፌ ላይ ከከተብኳቸው ሀሳቦች አንዱን አንስተው እንዲህ ሲሉ ጠየቁኝ ‹አእምሮ እውነትን ሲጸንስ ልብ ሀገርን ይወልዳል› ብለሃል ምን ማለት ነው ሲሉ። እኔም እንዲህ ስል መለስኩ.. ልብ ሀገርን ለመውለድ አእምሮ ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሊያውቅ ይገባል። አእምሮ ሀገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲያውቅ ከዘረኝነትና ከብሔር አስተሳሰብ የጸዳ ማንነት ያሻዋል።

ስለብሔርና ስለዘር በሚያስብ አእምሮ ውስጥ ሀገር የለችም። ሀገር ያለችው ሰላምና ፍቅርን በሚጠይቅ አእምሮ ውስጥ ነው። ስለማይረቡ ነገሮች እያሰብን የሚረቡንን ነገሮች አናገኝም። ስለማይጠቅሙን ነገሮች እያሰብን የሚጠቅሙንን ነገሮች አንደርስባቸውም። በአእምሯችን ምናምንቴ እያሰብን በልባችን በኩል ሀገራችንን መፍጠር አንችልም። ስለጥላቻ እያሰብን ሰላም ማምጣት አንችልም ስል መለስኩ።

ከፍቅርና ከሰላም የቀደመ ምንም ነገር እንዳይኖረን አድርገን ራሳችንንና ሀገራችንን እንፍጠር። በልባችን በኩል ሀገራችን እንድትወለድ ለሀገራችን የሚመች አእምሮን እናዳብር። ስለ ሰላምና ሰላም ስለሆኑ ነገሮች ብቻ እናስብ። ዓለም ላይ ያሉ ሀገራት ሁሉ በዜጎቻቸው አስተሳሰብ ልክ የተፈጠሩ ናቸው።

የአሁኗ ኢትዮጵያ በእኔና በእናንተ አስተሳሰብና ድርጊት የተፈጠረች ናት። ለሁለት አመታት ጦርነት ውስጥ ነበርን፣ ስለብሔርና ዘረኝነት ስናቀነቅን ኖረናል፣ ምክክርና ውይይትን ተጸይፈን በአልሸነፍ ባይነት ውስጥ ነበርን፣ ብቸኛው የሰላም መገኛ ጦርነት እንደሆነ አምነን ተቀምጠን ነበር። እኚህ ሁሉ አስተሳሰቦቻችን የአሁኗን ኢትዮጵያ ፈጥረዋታል። መጪዋ ሀገራችን በሀሳብና በሰላም እንደተፈጠሩ ሌሎች የዓለም ሀገራት በስልጣኔና በብልጽግና ወደፊት እንድትገሰግስ ስለሰላም ብቻ ልናስብ ይገባል።

ተሰርቶ ያለቀ ሀገር፣ ተሰርቶ ያለቀ ትውልድ የለም። ሀገር ቀን በቀን ነው የምትሰራው። ትውልድ ቀን በቀን ነው የሚቀረጸው። ሀሳቦቻችን ሁሉ ወደሰላም የሚወስዱንና ሰላም አምጪ ሊሆኑ ይገባል። ከብዙ ሞት በኋላ፣ ከብዙ እልቂት በኋላ ፖለቲከኞች ይታረቃሉ። ከብዙ ውድመት በኋላ፣ ከብዙ ክስረት በኋላ ሰላም ይመጣል።

ይሄ እውቀት አይጠይቅም። ይሄ መቼም በማንም መሆን የሚችል ነገር ነው። እውቀት የሚጠይቀውና አስተዋይ ሊያስብለን የሚችለው ከመሞታችን በፊት የሚያኖረንን ሰላም፣ ከመጎሳቆላችን በፊት የሚያበረታንን ፍቅር፣ ከመለያየታችን በፊት አንድ የሚያደርገንን ሰላም የእኛ ስናደርግ ነው። እዚህ ነገር ላይ ስንበረታ አንታይም። ታሪኮቻችን ሁሉ ከጦርነት በኋላ እርቅን፣ ከብዙ ሞቶች በኋላ መተቃቀፍን የሚያሳዩ ናቸው። ሳንሞት ሞትን የሚገል ሰላም ያስፈልገናል። ጥላቻን፣ መለያየትን የሚያጠፋ አንድነት ግድ ይለናል። የሄድንባቸውን የመከራና የጦርነት ጊዜያቶች ላለመድገም ዋስትና የሚሆኑ ስራ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ሁሉንም አይነት መስዋዕትነት ከፍለን ኢትዮጵያ ሀገራችን በአስተማማኝ ሰላም ውስጥ፣ በአስተማማኝ አንድነት ውስጥ፣ በአስተማማኝ ወንድማማችነት ውስጥ የምትሆንበትን ሰላም መፍጠር አለብን።

ይሄ ሰላም፣ ይሄ አንድነት፣ ይሄ ወንድማማችነት፣ ይሄ መተማመን በመካከላችን ካልተፈጠረ ዘመን ጠብቀው፣ የምርጫ ጊዜ ጠብቀው የሚመጡ አንዳንድ ነውጦች አይጠፉም። በምንም ነገር የማይላላ የሰላምና የእርቅ መሰረቶችን መገንባት አሁን ካለነው ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ከጦርነት በኋላ ሳይሆን ከጦርነት በፊት ስላለው ሰላምና ተግባቦት፣ እርቅና ምክክር እውነትና ቁርጠኝነት ሊኖረን ይገባል። ሞተንና ገለን፣ ተጋፍተንና ተለያይተን የምናገኘው ሰላም ምን አይነት እንደሆነ እናውቀዋለን። አሁን የሚቀረን ሳንሞትና ሳንገል፣ ሳንጋፋና ሳንለያይ ለሰላም መቀመጥ ነው።

ችግር የሆነብን ከስቃዮቻችን በፊት ችግሮቻችንን ለመፍታት ለውይይት አለመቀመጣችን ነው። ብዙ ነገሮቻችን ከተበላሹ በኋላ ለምክክር የምንቀመጥ ነን። ይሄ አስተሳሰብና ይሄ የሕይወት ልምድ ነው ዛሬ ላይ ሀገራችንን ኋላ ያስቀራት። ይሄ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነው ዛሬ ላይ ከድጡ ወደ ማጡ እያስገባን ያለው።

ፖለቲከኞቻችንም ሆነ ፖለቲካችን መፈተሽ አለበት። እየሄድን ያለው መንገድ ከጦርነት በኋላ ሰላም የሚል ከሆነ ቆም ብለን ማሰብ አለብን። የሚበጀን ከጦርነት በፊት ሰላም፣ ከጦርነት በፊት እርቅ፣ ከጦርነት በፊት አንድነት ነው። ቀጣይ ኢትዮጵያን የመፍጠርና የማሻገር ህልማችን ከዚህ ከችግሮቻችን በፊት ለሰላም መቀመጥ ከሚለው ጽንሰ ሀሳብ ቢጀምር እላለሁ። ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ የሚባለው ብሂል ከእንግዲህ መቆም አለበት።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዚህ ዘመን በማይመጥኑ አስተሳሰቦች መዳፏ ሊያበቃ ይገባል። አንድ ነገር ካልጠቀመንና ካልቀየረን እንድቀይረው የስነ ልቦና ባለሙያዎች ይመክራሉ። አንድ ነገር የምንፈልገውን ሰላምም ሆነ ሌላ ነገር ካልሰጠን አቅጣጫችንን ቀይረን ሌሎች ነገሮችን መሞከር እንዳለብን የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክሩናል። ከጦርነት በኋላ ሰላም ጠቅሞን አያውቅም። ከችግሮቻችንና ከመከራዎቻችን በፊት እርቅና መተቃቀፍ አሻግረውን አያውቅም። ለእንግዲሁ ከጥፋቶቻችን በመማር ከችግሮቻችን በፊት እንዴት ሰላም ማምጣት እንዳለብን በመምከር ስልጣኔአችንን መጀመር አለብን።

ከሞትን በኋላ፣ ብዙ ነገሮቻችንን ካጣን በኋላ የምንጮኸው መጮህ የምንለፋው ልፋት ዋጋ የለውም። አንድ ነገር ከመሆኑና ዋጋ ከማስከፈሉ በፊት እንዴት መቆጣጠር እንዳለብን ማወቁ ነው ህልሞቻችንን ወደመሆን የሚያመጣቸው። ሊለውጠንና ሊቀይረን በሚችል ሃሳብና ሙግት ላይ እንጂ ሊያከስረንና ዝቅ ሊያደርገን በሚችል ሀሳብና ሙግት ላይ ጊዜያችንን ማጥፋት አይኖርብንም። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፎ ከመስጠት ጋር አንድ ነው።

ዛሬም ትናንሽ አሉባልታና ሰላም ለማደፍረስ የማይበቁ ትናንሽ ሀሳቦችን እየነዙ ወደነበርንበት የጦርነት ሜዳ ሊመልሱን የሚፈልጉ አንዳንድ ኃይሎች ከዚህም ከዛም አሉ። ዳግመኛ ወደ ጦርነት እንዳንሄድ፣ ዳግመኛ ወደ መለያየት እንዳንሳብ የጥልን ግድግዳ የሚያፈርስ የፍቅር ምኩራብ መገንባት አለብን። ዳግመኛ ጦር እንዳናነሳ፣ ዳግመኛ እንዳንገፋፋ በመካከላችን ፍቅር የነሱንን ቁርሾዎቻችንን ተነጋግረን መፈታት አለብን።

እኔ በግሌ ከጦርነቱ በፊትም ሆነ በኋላ ብዙ ነገር ታዝቤአለሁ። አሁን እንኳን የሰሞኑን የሰላም መውረድ ተከትሎ አንዳንድ መቀመጫቸውን ውጭ ሀገር ያደረጉ፣ የኢትዮጵያን ሰላም የማይፈልጉ፣ ሁሌ ስንባላና ስንጋደል እንድንኖር የሚፈልጉ ግለሰቦች በሰላማችን ላይ ውሃ ለመቸለስ አሉባልታ ሲነዙ እየተደመጠ ነው።

መንግስት ከሕወሓት ጋር በገባው አስር ነጥብ ባለው ቅድመ ሁኔታ ላይ ተንተርሰው የማይሆን ነገር በመናገር ያገኘነውን ሰላም ለማጠልሸት የሚሞክሩ ድምጾች እየተሰሙ ነው። እኚህ ድምጾች የነበሩ ድምጾች ናቸው.. በነዚህ ድምጾች ላይ ተረማምደን ነው ሰላማችንን የመለስነው። በነዚህ ድምጾች ላይ ተረማምደን ነው ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ ያደረግነው። ወደኋላ ማየትም ሆነ መመለስ የማይታሰብ ነው።

በብዙ ጸሎትና ምኞት የመጣ ሰላማችንን መጠበቅና ማስቀጠል ከመንግስት ብቻ፣ ከተፎካካሪ ፓርቲ ብቻ፣ ከአፍሪካ ህብረት ብቻ የሚጠበቅ ሳይሆን ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ታላቅ የቤት ስራ ነው። አእምሯችንን ከዘረኝነት አጽድተን፣ በሀሳባችንና በተግባራችን ኢትዮጵያ የምትፈልጋቸው ሆነን ከሰላም ጋር፣ ከእርቅ ጋር፣ ከአንድነት ጋር ወደፊት መሄድ ቀሪ ተግባራችን ሊሆን ይገባል። ከላይ ባስነበብኳችሁና ይዤው በመጣሁት ‹ከጦርነት በፊት ሰላም› በሚል አዲስ መፈክር ጦርነት የሌለባትን፣ ሞትና ስደት የሌለባትን፣ መለያየትና መገፋፋት የሌለባትን ኢትዮጵያ እንፍጠር ።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ከዓሣ ሀብት የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን - የምርምር ማዕከሉ ድርሻ

**ስምስም መንግሥቱ**



በኢትዮጵያ ከእንስሳት ልማት ዘርፍ አንዱ በሆነው የዓሣ ሀብት በዓመት ከ90ሺ ቶን በላይ ዓሣ ማምረት እንደሚቻል መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከሀይቆች ጣና፣ ዝዋይ፣ አባያ፣ ጫሞ፣ ሀዋሳ፣ ከወንዞች ባሮ፣ ከግድብ ተከዜ በመሳሰሉት የውሃ ሀብቶች ውስጥ ዓሣ ማስገር የሚያስችል እምቅ ሀብት መኖሩን እነዚሁ መረጃዎች ያመለክታሉ።

የዓሣ ልማትን ጨምሮ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት በመጨመር የግብርናውን ዘርፍ ከፍ በማድረግ እንደ ሀገር በምግብ ፍጆታ ራስን ለመቻል፣ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በመንግሥት በኩል ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ይገኛል። ጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ላይ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይፋ የተደረገውንና ለአራት ዓመታት የሚተገበረውን የሌማት ትሩፋት ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የእንስሳት ሀብት ልማት በቅንጅት ከተከናወነና በቴክኖሎጂ ከታገዘ አማራጭ የምግብ ግብዓቶችን ማብዛት እንደሚቻል መርሃ ግብሩን በይፋ ያስጀመሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መግለፃቸው ይታወሳል። በዚህ መርሃ ግብር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና ሥርዓተ ምግብን ማሻሻል እንደ ዋነኛ ዓላማ መያዙንም አመላክተዋል።

መርሃ ግብሩ ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ሀገራዊ ንቅናቄ ተፈጥሮ ወደ ሥራ ተገብቷል። መርሃ ግብሩን ስኬታማ ለማድረግም የምርምር ማዕከላት የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከፍ ያለ ሚና ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ የዓሣ ጫጩቶችን በምርምር በማበዛትና ተደራሽ ለማድረግ ሰበታ ዓሣ ምርምር ማዕከል በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት መካከል ነው።

በኢትዮጵያ ስላለው የዓሣ ሀብትና ጥቅም ላይ በማዋል በኩል በተለይም በሰበታ ምርምር ማዕከል እየተከናወነ ስላለው ተግባር ያነጋገርናቸው የምርምር ማዕከሉ ተመራማሪ ዓለማየሁ ውቤ እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ ከ200 አይነት በላይ የዓሣ ዝርያዎች ይገኛሉ። ነገር ግን በዓሣ ዝርያ በግብርናው ዘርፍ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት ከአምስት አይነት የዓሣ ዝርያዎች አይበልጡም። በህብረተሰቡ ዘንድም የሚታወቁት እጅግ ጥቂቶቹ ሲሆኑ፣ በስፋት የሚታወቁትም ቆሮሶና አምባዛ የተባሉት ዝርያዎች ናቸው።

በምርምር ማዕከሉ የተለያየ ዝርያ ያላቸውን የዓሣ አይነቶች የማራባት ሥራ ይከናወናል። በምርምር የተራባው ዓሣ እንዲለማ ደግሞ ጫጩት ዓሣዎችን ለአርሶ አደሮችና ጥያቄ ለሚያቀርቡ የተለያዩ አካላት ወይንም አልሚዎች ማዕከሉ ያቀርባል። የሚሰራጩት ጫጩት ዓሣዎች እንደ ኃይል ማመንጫ እና ለተለያየ የግብርና ሥራ በሚውሉ የመስኖ ግድቦች ውስጥ ሊለሙ የሚችሉ ናቸው። ጫጩቶቹም የገበያውን ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ ናቸው።

ጫጩት ዓሣዎችን በተጠቃሚው ፍላጎት መሠረት ለማቅረብ በተደረገው ጥረት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የደንበኛ ፍላጎት ማሟላት መቻሉን የጠቆሙት ተመራማሪው፤ በቅርቡም ሐረር አካባቢ ወደ አምስት ሺህ ጫጩቶች መሰራጨታቸውን ነው የገለጹት። ከግብርና ሚኒስቴር በቀረበ ጥያቄ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያም "ቆሮሶና ካርፕ" የተባለ ዝርያ ያላቸው ወደ አስር ሺ ጫጩት ዓሣዎች መሰራጨታቸውን አመልክተዋል።

በተለይ በግብርና ሚኒስቴር በኩል የሚቀርቡ የጫጩት ዓሣ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙት በሰበታ ምርምር ማዕከል በኩል እንደሆነም ተመራማሪው ጠቁመዋል። ማዕከሉ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በማሟላትም የመጀመሪያው የመንግሥት ተቋም እንደሆነ ጠቁመዋል።

ዓሣ በወንዞች ብቻ የሚገኝ አለመሆኑን የሚናገሩት ተመራማሪው፣ አንዳንድ ግድቦች የወንዝ ዓሣ ሊኖራቸው እንደሚችል ግን ይገልፃሉ። ነገር ግን የዓሣ ዝርያው ለምግብነት የማይውል ሊሆን እንደሚችልም ይናገራሉ። እንዲህ ያለው ነገር ሲያጋጥም በምርምር ማዕከሉ ተፈልፍለው የወጡ ለምግብነት የሚውሉ የዓሣ ዝርያዎች በግድቡ ውስጥ እንዲረቡ ይደረጋል ይላሉ። የወንዝ ዓሣዎች ደግሞ በአብዛኛው ሥጋ እንደሌላቸውና አጥንት እንደሚበዛባቸው ነው ያብራሩት። ገበያ ላይ ያላቸው ተፈላጊነትም አነስተኛ እንደሆነም ተናግረው፣ እንደየሁኔታውና አስፈላጊነቱ በምርምር የተፈለፈሉ የዓሣ ዝርያዎች ለግድቦች እንደሚያስፈልጉ አስታውቀዋል።

በሀይቅ ላይ የተለየ ሁኔታ መኖሩንም ተመራማሪው ይጠቁማሉ። የመጥመጃ ቦታን ዝግ በማድረግና እንዳይጠመድም ክልከላ ከተደረገ በውስጡ ያሉት ዓሣዎች ራሳቸውን መተካትና መፈልፈል እንደሚችሉም ይገልጻሉ። ኩሬዎችና አዳዲስ ግድቦች ላይ ግን የመጀመሪያ መነሻ ዘር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ ማዕከሉም መነሻ ዘር በማሰራጨት እርባታው እንዲስፋፋ ያደርጋል ይላሉ።

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በኢትዮጵያ የዓሣ ምርት አቅርቦት አነስተኛ እንደሆነና በዋጋም ውድ መሆኑ ይነገራል። በሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁ ይነሳል። የዓሣ ዝርያዎችም እየጠፉ እንደሆነም በስፋት ይነገራል። ይህ ለምን ሆነ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ተመራማሪው በሰጡት ማብራሪያም፤ የዚህ ምክንያቶቹ ብዙ መሆናቸውን ይገልፃሉ። የተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመርና ፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን አንዱ ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ። ሌላው ደግሞ ሙያዊ ጉዳይ ነው ይላሉ። በዚህ ረገድም ዓሣን ለማጥመድ የሚውል የመረብ አጠቃቀም ለጉዳቱ ምክንያት መሆኑን ይጠቅሳሉ። ማጥመጃ መረብ መምረጥ ካልተቻለ የዓሣ ዝርያን የሚያጠፋ መረብ እንዳለም ጠቁመው፣ ይህንን ማስወገድ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ተመራማሪው እንዳሉት፤ ይሄ የዓሣ ዝርያን በማጥፋት ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል ተብሎ የሚገመተው የመረብ አይነት ነው በኢትዮጵያ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው። መረቡ በግዥ ከውጭ የሚገባ ሲሆን፣ በዋጋ ርካሽ በመሆኑ ነው አብዛኛው ዓሣ አጥማጅ የሚጠቀመው። መረቡ አንዴ ዓሣዎቹ በሚገኙበት ሀይቅ ወይንም ግድብ ላይ ሲጣል ከጫጩት እስከ ትልቅ ዓሣ ይይዛል። በዚህ ጊዜም ሁሉንም ሳይመርጥ ይገላቸዋል። በዚህ መረብ የማጥመድ ድግግሞሹ ሲኖር ደግሞ ተተኪ ዓሣዎች ይጠፋሉ። መመናመኑ በዚህ መንገድ ይፈጠራል።

ሌላው ለዓሣ ሀብት መመናመን ምክንያት የሆነው በሕገወጥ መንገድና ኃላፊነት በጎደላቸው ዓሣ አጥማጆች በሚደርስ ጉዳት እንደሆነ የጠቆሙት ተመራማሪው፤ እነዚህ አካላት መቼና እንዴት እንደሚያጠምዱ ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ በሆነበት ሰዓት የማጥመዱን ሥራ ስለሚያከናውኑ መከላከል ባለመቻሉ በዓሣ ሀብት ላይ ጉዳት እየደረሰ መሆኑን ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አብዛኞቹ ሀይቆች ማንም ተነስቶ መረቡንና ጀልባውን ይዞ ለመግባት የሚችልባቸው ለሁሉም ክፍት የሆኑ ናቸው። በዚህ ስፍራ የሚካሄደው ዓሣ የማጥመድ ስራም ይሄን ያህል አጥማጅ አለው ወይንም በዚህ መንገድ ዓሣ መጠመድ አለበት የሚል ሳይንስን ተከትሎ የሚከናወን አይደለም።

አንዳንዴ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ሲባል ከአቅም በላይ ጫና የሚፈጠርበት ሁኔታ በስፋት እንደሚስተዋልም ነው ተመራማሪው ያስገነዘቡት።

> **በምርምር ማዕከሉ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን የዓሣ አይነቶች የማራባት ሥራ ይከናወናል። በምርምር የተራባው ዓሣ እንዲለማ ደግሞ ጫጩት ዓሣዎችን ለአርሶ አደሮችና ጥያቄ ለሚያቀርቡ የተለያዩ አካላት ወይንም አልሚዎች ማዕከሉ ያቀርባል። የሚሰራጩት ጫጩት ዓሣዎች እንደ ኃይል ማመንጫ እና ለተለያዩ የግብርና ሥራ በሚውሉ የመስኖ ግድቦች ውስጥ ሊለሙ የሚችሉ ናቸው**

በዚህ መልኩ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ማህበራትም አላስፈላጊ መረቦችን መጠቀም ብቻ ሳይሆን በዓሣዎቹ የመራቢያ ቦታዎችም ላይም ጭምር በማጥመድ ጉዳቱን የሚያባብሱበት ሁኔታ እንዳለም ይናገራሉ። እንዲህ ላለው ችግር በተለይ በስምጥ ሸለቆ አካባቢ ያሉ ሀይቆች ተጋላጭነታቸው ሰፊ መሆኑን ይጠቁማሉ።

የዓሣ ሀብት ልማት በዚህ ዓመት መተግበር በጀመረው የሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብር ከእንስሳት ሀብት ልማት አንዱ በመሆኑ ዘርፉን ከተለያየ ጉዳት በመጠበቅ በልማቱ ውስጥ ድርሻ እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በተለይም ማዕከሉ ዓሣዎችን በማራባትና ጫጩቶችንም ከማሰራጨት ባለፈ በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችንም ከነመፍትሄው በጥናት ለይቶ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ረገድ ያከናወነው ተግባር ይኖር እንደሆን ተመራማሪው ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ማዕከሉ ዘር ከማውጣትና ከማሰራጨት በተጨማሪ መረጃ በማውጣት ለፖሊሲ አውጭዎች እንዲደርስ ያደርጋል ብለዋል።

ተመራማሪው እንዳሉት፤ ከአንድ ሀይቅ በዓመት ምን ያህል ዓሣ ሊመረት እንደሚችል፣ መሰማራት ያለባቸው ዓሣ አጥማጆችና ለማጥመጃ የሚውል የመረብ ብዛት በምርምር ማዕከሉ ተመራማሪዎች በየጊዜው ተተንትኖ መረጃ ይወጣል። በአሁኑ ጊዜም በኢትዮጵያ በዓመት ወደ 94ሺ ቶን የሚሆን ዓሣ እንደሚመረት መረጃው የተሰጠው ከሰበታ ምርምር ማዕከል ነው።

ዓመታዊ ምርቱ ብዙ ቢሆንም የዓሣ ምርት አሁንም ከውጭ በግዥ የሚገባበት ሁኔታ መኖሩን በመጥቀስ ለተመራማሪው ለቀረበላቸው ጥያቄ "ይሄ የዓሣ ሀብት ያለባቸውን አካባቢዎች ጠንቅቆ ካለማወቅ የሚመጣ ችግር ነው" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከዓሣ ምርት ጋር በተያያዘ ስምጥ ሸለቆ እና ባህርዳር አካባቢ ያለው ብቻ ነው ትኩረት የሚደረግበት፤ ነገር ግን መሠረተ ልማት ባልተሟላባቸው ከከተማ በርቀት ላይ በሚገኙ የሀገሪቱ ክፍሎች የዓሣ ሀብቱ በስፋት አለ። ለምሳሌ አፋር ክልል ደረቅ የሆነ የአየር ፀባይ ያለው በመሆኑ ለዓሣ ልማት ይሆናል ተብሎ እንደማይታሰብ አንስተው፤ ነገር ግን ከሰባትና ስምንት ያላነሱ ግድቦችና ሀይቆች ያለበት መሆኑን ይጠቁማሉ። በዚህም በስፋት ዓሣ ማልማትና ማሟላት እንደሚቻል ይገልፃሉ። በዚህም ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚቻል ጠቅሰው፣ በአካባቢው ግን ዓሣ እየለማ አለመሆኑን ይናገራሉ። ማእከሉ የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ የያዘ የተሟላ መረጃ አውጥቶ ለሚመለከተው አካል ማቅረቡንም ነው የጠቆሙት።

"የአካባቢ ሀብት በጥናት ተለይቶ ዝግጁ ሲሆን ተከታትሎ ወደ ተግባር ማዋል የአስፈጻሚው አካል ድርሻ ሊሆን ይገባል" ያሉት ተመራማሪው፤ የመሰረተ ልማት ተደራሽነት ትኩረት ቢሰጠው ልማቱ ይፋጠናል የሚል እምነት አላቸው። በዓባይ ግድብም አንዴ የዳሰሳ ጥናት በምርምር ማዕከሉ መደረጉን ጠቅሰዋል። በማዕከሉ እገዛ በአካባቢው ላይ የዓሣ ልማት እንደሚካሄድ ጠቅሰው፣ ስራው ግን በቂ እንዳልሆነ አመልክተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የግድቡ አካባቢ ትልቅ መስህብ እንደሚሆን የሚጠበቅ በመሆኑ ወደፊት የዓሣ ጫጩት ማስፈልፈያ፣ የምርምር ማዕከልና መቋቋም እንዳለበት የዘርፉ ተመራማሪዎች እምነት ነው። ለሚከናወነው ልማትም ዩኒቨርሲቲዎችም ተሳታፊ ቢሆኑ ውጤታማ እንደሚሆንም ምክረ ሀሳብ ሰጥተዋል፡

**እንደ መውጫ**

ኢትዮጵያ በቀንድ ከብትና በተለያየ የእንስሳት ዝርያ ትታወቃለች። ይሁን እንጂ በግብርናው ዘርፍ በስፋት እየተከናወነ ያለው በሰብል ልማት ላይ ነው። የእንስሳት ሀብት ልማቱ ገበያ ተኮር ባለመሆኑ አርሶ አደሩ በመንደሩ እያረባ ያለው ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣ የቀንድ ከብት እንዲሁም የዓሣ ልማት በአጠቃላይ የእንስሳት እርባታ ከእለት ከፍጆታ ያለፈ አይደለም። ይህ መሆኑም ዘርፉ እንደሀገር በክፍለ ኢኮኖሚው ላይ የሚጠበቀውን ያህል ድርሻ እንዳይኖረው እንዳደረገው በተለያየ ጊዜ በሚካሄዱ መድረኮች ሲገለጽ ይሰማል።

ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የእንስሳት ልማቱን ለማሳደግና ውጤቶችንም ከፍ ለማድረግ በመንግሥት በኩል ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸው ይታወቃል። በተለይም በዶሮ እርባታና በወተት ልማት በተከናወኑት ተግባራት መልካም የሚባል እንቅስቃሴ ታይቷል። በተለይም እሴት የተጨመረበት የወተት ልማት እየተለመደ መጥቷል። ልማቱ ተጠናክሮ የበለጠ ውጤት እንዲያስገኝ በማድረግ ረገድ አሁንም ሥራዎች ይቀራሉ።

እንደ ሀገር የተያዘው የሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብር እንዲሳካ ከምርምር ተቋማት የሚገኙ የምርምር ውጤቶችና ምክረ ሀሳቦች ጠቃሚ እንደሆኑም ከሰበታ ምርምር ማዕከል እንቅስቃሴ መገንዘብ ይቻላል።

ሀገሪቱ በርካታ ሀይቆችና ትላልቅ ጅረቶች ያሏት ከመሆኑ በተጨማሪ ለተለያዩ ስራዎች የሚገነቡ ግድቦች ባለቤትም ናት። ይህን መልካም አጋጣሚ ከዓሣ ልማት ጋር በማስተሳሰር መስራት ይገባል። ለእዚህ ደግሞ የሰበታ ዓሣ ምርምር ማእከል ፋይዳ ከፍተኛ ነው።

# የትምህርቱ ዘርፍ አመራሮች የጎለበቱበት ስልጠና

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

መምህር ፍቅሬ ሀብቴ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የቡልቡላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው። በመምህርነትና በርዕሰ መምህርነት ለ21 ዓመት አገልግለዋል። በዚህ ቆይታቸው በሁለተኛ ዲግሪ ስኩል ሊደርሽፕ ትምህርትን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተከታትለዋል። ሆኖም የተማሩትን መሬት ላይ ለማውረድ ይቸገሩ ነበር። ለዚህ ምክንያት የሆነው ደግሞ እንደ ሀገር የነበረው ምልከታና የአሰራር ሁኔታ የፈጠረው መሰላቸት የራስ ተነሳሽነት እንዲጠፋ ማድረጉ ነው።

እንደ መምህር ፍቅሬ ሃሳብ፣ የርዕሰ መምህርነት ሥራን የአስተዳደር ሥራ ብቻ አድርጎ የመቁጠር ዝንባሌ መማር ማስተማሩን በመደገፉ በኩል እምብዛም እንዲሰራበት ሲያደርግ አይታይም። ርዕሰ መምህር የሚመረጥበት መንገድም ከሙያ ይልቅ ፖለቲካ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለዚህ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

አሁን ግን ሁኔታዎች እየተቀየሩ መምጣታቸውን የጠቀሱት መምህር ፍቅሬ፣ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት የተለያዩ ስልጠናዎችና ክትትሎች እየተደረጉ እንደሚገኙ ይናገራሉ። ለዚህም ማሳያ አድርገው የሚያስቀምጡት በእንግሊዝ መንግስት ድጋፍና በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት Education Development Trust (EDT) የተሰኘ ስልጠና ማግኘታቸውን ነው። ‹‹ዛሬ ለምረቃ የበቃንበት የተግባር ትምህርት ከንድፈ ሀሳብ ያየለበት ስልጠና ነው›› ያሉት መምህር ፍቅሬ፣ መሰል ስልጠናዎች የርዕሰ መምህርነት ሥራ በእውቀት እንዲመራ ያግዛል ብለው ያምናሉ፡፡

ስልጠናው አዳዲስ ሀሳቦችን እያመነጩ ለሀገር የሚተርፉበትን መንገድ ያመላከታል የሚሉት መምህር ፍቅሬ፣ በተለይም ትምህርት ቤቶች ከፖለቲካ አመራር ተለይተው እንዴት በእውቀት ከሙያው ጋር ተሰናስለው መመራት አለባቸው የሚለውን ጉዳይ ለማየት ስልጠናው እንደሚረዳ ያስቀምጣሉ። ይህ ስልጠና መምህራንን ደግፎ፣ ማህበረሰቡን አሳትፎና ተማሪዎችን በተሻለ እውቀት አንጾ እንዴት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል በሚገባ የሚያረጋግጥም እንደሆነም ያነሳሉ።

እንደ ርዕሰ መምህሩ ገለፃ፣ መሰል ስልጠናዎች ተወዳዳሪ ትምህርት ቤት ከመፍጠር አኳያም የማይተካ ሚና አላቸው። ስኩል ሊደር ያልተማሩ መምህራንም ቢሆን ጥሩ እውቀት ይጨብጡበታል። በዚህም ቀጥታ ከመምህርነት ወደ ርዕሰ መምህርነት የሚገቡ ባለሙያዎችን በተለመደው አሰራር ከመያዝ ይታደጋቸዋል።

መምህር ፍቅሬ እስከዛሬ በነበረው ልምዳቸው ከእቅድ ጀምሮ ያለው ሁኔታ ትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ አለመሆኑን ይናገራሉ። አሁን ግን ከተለመደው አሰራር ወጥተው በራሳቸው አዳዲስ ነገር እየፈጠሩ እንዲጓዙ ስልጠናው እድል የሚፈጥር መሆኑን ያስረዳሉ።

ቀደም ሲል የነበረው አሰራር ሱፐርቫይዘር ሳይቀር ግብረ መልሶችን ሲሰጥ በዘልማድ እንጂ በእውቀትና ትምህርት ቤቱን እንዲሁም መምህሩን በሚያሻሽልበት ሁኔታ አልነበረም። እናም ይህ ስልጠና መሰል ክፍተቶችን ይሞላል የሚል እምነት እንዲኖራቸው አድርጓል። ከዚህ ባሻገር ይህ ስልጠና እንደ ሀገር ከርዕሳነ መምህራን አንጻር በተለይ ሴቶች ላይ መስራት ቢቻል ብዙ ውጤታማ የሚያደርግ ነው ሲሉም ይናገራሉ።

ይህንን ሲያብራሩም፣ ‹‹ሴት ርዕሰ መምህራን ትምህርት ቤቶችን ሲመሩ ከቤታቸው አይለዩም። በእውቀትና በአሰራር የተሻሉም ናቸው። ለዚህ ማሳያው ደግሞ ሴቶች የሚመሯቸውን ትምህርት ቤቶች ብቻ መመልከት ነው። እናም ልምዳቸውንና አቅማቸውን የሚያሳድጉበት እንዲህ አይነት ስልጠና እጅግ ያስፈልጋቸዋል። ወንዶችን በልጠው ተወዳዳሪ ሴት አመራሮችን የሚፈጥሩበትን እድልም ይሰጣቸዋል፡፡›› ይላሉ። በዚህ ረገድ ትምህርት ሚኒስቴርም የጀመረውን ስልጠና ማስፋት እንዳለበት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

መምህር ፍቅሬ ሴቶች በእንዲህ አይነት ስልጠናዎች (በኢዲቲ) ሲደገፉ ጥሩ የመማር ማስተማር ሁኔታን ከወንዱ በላቀ መልኩ ይፈጥራሉ የሚል ሃሳብ አላቸው። ነገር ግን ይህ ሥራ ለትምህርት ሚኒስቴር ወይም ለክልል ትምህርት ቢሮዎች ብቻ የሚተው ሳይሆን እንደ ትምህርት ቤትም የሚሰራበት ሊሆን እንደሚገባ ያስቀምጣሉ።

ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት ኃላፊነትን እንዲለማመዱና እድሉን እንዲያገኙ በተለያየ ዘርፍ ላይ ማበረታታት ያስፈልጋል። ለአብነት የትምህርት ክፍሎች ተጠሪ፣ የክበባት መሪዎች፣ በተማሪ በኩል ደግሞ የክፍል አለቆች እያደረጉ ወደፊት ማምጣት ያስፈልጋል። ይህም ሲያድግ መምራት እንችላለን ብለው እንዲያምኑ ያደርጋል። በዚህም ርዕሰ መምህርነትን ኃላፊነት ተወዳድረው በብቃት እንዲያገኙና የሀገር ተስፋ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል የሚል ሀሳብ እንዳላቸው መምህር ፍቅሬ ይናገራሉ።



ፎቶ፡- ምህረት

በስልጠና የትምህርት ቤት አመራሮችን ሚና ማሳደግ አስፈላጊ ነው፣

ለተከታታይ ስምንት ወር የተሰጠው ይህ ስልጠና፤ በዩኒቨርሲቲ ኢንስትራክተሮች እገዛ ተግባር ተኮር ሆኖ የቀጠለ ነው። ይህም እነ መምህር ፍቅሬ በርካታ ለውጦችን በትምህርት ቤታቸው ውስጥ እንዲያመጡ አስችሏል። ለአብነትም የአመራር ስርዓት መቀየር አንዱ ነው። ከወላጆችና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር አብሮ ለመስራት የሚደረገውም ጥረት የስልጠናው ውጤት ነው።

ለርዕሰ መምህራኑ የተሰጠው ስልጠና ተጨባጭ ውጤት ያመጣ እንደሆነ በየክልሉ ያሉ ትምህርት ቢሮዎች ተሞክሯቸውን በሚያካፍሉበት ጊዜ ለመገንዘብ ተችሏል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የሲዳማ ክልል ትምህርት ቢሮ ነው። የክልሉ ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ተክሉ አዱላ፤ ስልጠናው የትምህርት ማህበረሰቡን ከውጭው ማህበረሰብ ጋር በእጅጉ ያስተሳሰረ መሆኑን ይመሰክራሉ። ስልጠናው ማህበረሰቡ ለትምህርት ቤቱ ትምህርት ቤቱም ለማህበረሰቡ ምን ማበርከት እንዳለበትም ያሳየ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ተክሉ፣ አሁን ሁለቱ አካላት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆነዋል ይላሉ።

ይህ ለርዕሳነ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የተዘጋጀ ስልጠና በራስ አቅም መስራትን የገነባ ነው። ለዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር ስልጠና ውጭ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ጅምሩን የማስፋት ሥራ ሰርተዋል። ይህም የሚታይ ለውጥ አምጥቷል። ለዚህ አብነት የሚሆነውም ማህበረሰቡና ትምህርት ቤቶች አብረው የሚሰሩበትን እድል አመቻቸት መቻሉ ነው።

የኦሮሚያ ክልል በስልጠናው መጠቀሙን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ ይናገራሉ። ይህን ሲያብራሩም፤ ‹‹ስልጠናው በሰጠን እድል ከክልል ፕሬዚዳንቶች ጋር ሳይቀር መቀራረብና መሥራት ጀምረናል። በቋሚነት የምናሰለጥንበት ማዕከል ለመስራት አስበን በአዳማ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። ስልጠናው ለትምህርቱ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን አስተምሯል። አዳዲስ ሀሳቦችን ለማመንጨትም አስችሏል›› ይላሉ።

ከስልጠናው ጋር በተያያዘ በEducation Development Trust የሀገር አቀፍ የርዕሰ መምህራን ስልጠና ፕሮግራም አስተባባሪ ወይዘሮ ትዕግስት ተፈራ፣ ስልጠናው ከእንግሊዝ መንግስት በተገኘ ድጋፍ ላለፉት ሦስት ዓመታት ትምህርት ሚኒስቴር ሲተገበረው የቆየ መሆኑን ያስታውሳሉ። ይህ ደግሞ ብዙ መፍትሄዎችን ያመላከተ ከመሆኑ ባሻገር ቀደም ሲል የነበሩ ስልጠናዎችን ለመቃኘት እድል ሰጥቷል። ‹‹የቀደሙ ስልጠናዎች የሥራ ላይ ክህሎትን መሰረት ያደረጉ አልነበሩም። ዋና ትኩረታቸው ንድፈ ሀሳብ እንጂ ተግባር አይደለም። ይህ ደግሞ ስልጠናን ከሀሳብ እንዳያልፍ አድርጎታል›› ይላሉ አስተባባሪዋ ሲያብራሩ።

በተለያየ ዙር ለተለያዩ ሰልጣኞች ለተከታታይ ስምንት ወራት የሚሰጠው ይህ ስልጠና ርዕሰ መምህራን ሥራቸውን እያከናወኑ የወሰዱት ነበር። ይህ ደግሞ ትምህርት ሚኒስቴር ያስቀመጠውን መስፈርት ማሟላት የሚችሉ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸው ትምህርት ቤቶችን ያበራክታል ተብሎ ይጠበቃል። ከምንም በላይ ደግሞ በስነምግባር የታነጹና በአቅም የጎለበቱ እንዲሁም ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎችን ለማፍራት ያስችላል። የስልጠናው በአምስት ክልሎች ላይ በ40 ትምህርት ቤቶች የተጀመረ ሲሆን አመርቂ ለውጥ በማሳየቱ በሌሎች ክልሎች እንዲሰፋ ተደርጓል። አሁን ላይ በ500 ትምህርት ቤት ላይ ሥራው ተከናውኗል። ይህ ደግሞ 4ሺህ 500 ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን የስልጠና ተጠቃሚ አድርጓል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ 800 የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።

በመምህራን ደረጃ እንደ ሀገር 40 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። ሆኖም በርዕሳነ መምህራን ደረጃ ከ10 በመቶ አይበልጡም። ሴቶችን ወደአመራርነት ሊያመጣ የሚያስችል አሰራር አለመዘርጋቱ ደግሞ ለዚህ አንዱ ምክንያት ነው። ይህም እስከዛሬ የትምህርት ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው ስልጠና ላይ የሚሳተፉ ሴት ርዕሳነ መምህራንን ቁጥርን እጅግ አናሳ አድርጎታል። ለዚህም እንደ ሀገር በስልጠናው የተካፈሉ ሴቶች ከ12 በመቶ ልቆ አለመገኘቱ ተጠቁሟል። ትምህርት ሚኒስቴር ግን የሴት አመራሮችን ቁጥር ሃምሳ በመቶ ለማድረስ በዓመት እቅዱ አካቷል።

በዚህ ረገድ እየተተገበሩ በሚገኙ አንዳንድ ሥራዎችና በአስገዳጅነት በሚወጡ መመሪያዎች መሻሻሎች እየታዩ ናቸው። አንዱ በዚህ ስልጠና የታየው ነገርም ይህ ነው። የሴት አመራሮችን በብቃት ወደፊት ለማምጣት ሲባል ከየትምህርት ቤቱ ከሚላኩት ሰልጣኞች ውስጥ ቢያንስ አንዷ ሴት እንድትሆን ተደርጓል። በዚህም እንደ እቅድ አምስት መቶ ተይዞ ከዚያ በልጦ እየተገኘ ነው፡፡

በዚህ ስልጠና ብዙ ስኬቶች ተመዝግበዋል። አንዱ የስልጠናውን ጥቅም ተረድቶ በተግባር መተርጎም ሲሆን ሌላው የአስተዳደር ስራው ላይ ሰፊ ልዩነትና መሻሻል መታየቱ ነው። የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመደገፍም የተሻለ እድል ተፈጥሯል። መምህራንን የሚያግዙ፣ የመማር ማስተማር ሥራውን የሚመሩ፣ ለተማሪዎች አመቺ የትምህርት ቤት ምህዳር የሚፈጥሩ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ተባብረው የሚሰሩ፣ ትምህርት ቤት የሚመራው በግል ሳይሆን በጋራና በትብብር እንደሆነ የሚረዱ ርዕሳነ መምህራንንና ሱፐርቫይዘሮችን መፍጠር ተችሏል። የባህሪ ለውጥም አምጥቷል።

ሴቶችን ወደአመራርነት እንዳያመጡ ያደረጓቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ከሃይማኖት፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካና ባህል የሚጠቀሱ ናቸው። ስለዚህም የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት፣ የቅጥርና ምደባ ስርዓቱን ለሴቶች በሚመች መልኩ ማስተካከልና ሴቶችን ወደኋላ ሊጎትቷቸው የሚችሉ ነገሮችን ማቅለል ለችግሩ መፍትሄ እንደሆኑ ታምኖባቸው ወደሥራ መግባት እንደሚያስፈልግ በስልጠናው የተካፈሉ ሴቶች አስተያየት ሰጥተዋል።

መምህራንና ትምህርት አመራር ልማት ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ሙሉቀን ሙላቱ እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም የነበረው የትምህርት ቤት አመራር ንድፈ ሀሳባዊ ነው። በዚህም ርዕሰ መምህራን አስኳል የሆነውን የመማር ማስተማር ሥራ በመተው ፖለቲካው የሚያዛቸውን በመተግበር ይጠመዱ ነበር። ይህ ደግሞ አቅም ያላቸው መምህራን ወደፊት እንዳይመጡና ሙያውን እንዳይወዱት አድርጓቸዋል። ይህንን መቀየር የሁሉም ኃላፊነት መሆን አለበት።

አሁን በትምህርቱ ዘርፍ ሀገር የምትፈለገው ነገር የተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ መስራት ነው። ርዕሳነ መምህራን ደግሞ የዚህ ሥራ ዋነኛ ተዋናዮች ናቸው። ለስራቸው ራሳቸውን የሰጡ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ተወዳዳሪ የሆኑ የትምህርት ቤቶችም እንዲሁ። ስለዚህም አመራሮች አርቆ አሳቢ፤ አካታች የሆኑ ስራዎችን መስራት ይጠበቅባቸዋል። ትምህርት ቢሮዎች ደግሞ መደገፉ ላይ መበርታት ይኖርባቸዋል። ይህ ከሆነ ስልጠናው ተግባራዊ ይሆናል፣ ሀገርም ትለወጣለች።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው እንደዚህ አይነት ስልጠናዎች ለሁሉም የትምህርት ቤት አመራሮች እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን አስምረውበታል። በመሆኑም ሁሉንም በአንዴ መድረስ አይቻልምና በየጊዜው በስልጠናው የትምህርት ቤት አመራሮችን ሚና ማሳደግ አስፈላጊ ነው። ለዚህም ለርዕሳነ መምህራን ስልጠና የሚሰጥ ተቋም እንዲኖር ይደረጋል ሲሉ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ተናግረዋል። ‹‹የትምህርት ጥራቱን ለማስጠበቅ ፍላጎትና አቅም ያላቸውን ርዕሳነ መምህራንን ከማሰልጠን ባሻገር በአስተሳሰብ ላይ ጠንክሮ መስራት ያስፈልጋል። ስለሆነም መሰል ስልጠናን በስፋት የምንቀጥልበት ይሆናል›› ሲሉም ፕሮፌሰሩ በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ ተገኝተው ተናግረዋል።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ ፈተናዎችም ውስጥ ሆና ስተቸገሩ ከለላ መሆኗን ቀጥላለች››

**-የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋሁን ጎበዛ**

ምህረት ሞገስ



ጦርነት እና የተፈጥሮ አደጋ ገፍቷቸው ከአገራቸው ተሰደው ወደ አጎራባች አገራት ስለሚሰደዱ ሰዎች ሲነሳ አፍሪካውያን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። በተለይ ተደጋጋሚ የጦርነት ስጋት የሚንዣብብበት ምስራቅ አፍሪካ የስደተኞች ቁጥር በየጊዜው በአስር ሺዎች የሚቆጠር ሲሆን፤ በምስራቅ አፍሪካ የስደተኞች መዳረሻ ከሆኑት አገራት መካከል አንደኛዋ ደግሞ ኢትዮጵያ ናት።

በኢትዮጵያ ከውጭ ከሚገቡ ስደተኞች ጋር ተያይዞ ከሚሠሩ ተቋማት ዋነኛው የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ድርጅት ነው። ተቋሙ መቼ ተቋቋመ ከሚለው ጀምሮ እየሠራ ያለውን ስራ በሚመለከት እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም ወደ መሃል ከተማ እየገቡ ስለሚሠሩት ሰደተኞች ሕጋዊነት ጉዳይ አንስተን የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋሁን ጎበዛን ጠይቀን ምላሻቸውን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት እንዴት እና መቼ ተቋቋመ ከሚለው እንጀምር**

**አቶ ተስፋሁን፡-** ተቋሙ መቼ እና እንዴት ተቋቋመ የሚለውን ለመመለስ በአጠቃላይ ከስደተኛ ጋር በተያያዘ የአገራችን የህግ ሁኔታ እና የተቋማዊ ምላሽ ምን ይመስላል? የሚለውን መለስ ብሎ ማየት አስፈላጊ ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ስደተኞችን በመቀበል እና በማስተዳደር የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላትና ምናልባትም ለሺህ ዓመታት የተለያዩ ግጭቶችን በተለይም ጦርነትን ሸሽተው የሚመጡ ሰዎችን በማስጠለል የምትታወቅ ነች። ይህ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ሕግ ከመውጣቱም በፊት የነበረ ሂደት ነው።

ይህ መልካም እና ቀና ተግባር በሕግ ማዕቀፍ መደገፍ የጀመረው ደግሞ እ.ኤ.አ በ1951 ዓ.ም ነበር። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣው የስደተኞች ኮንቬንሽን (Refugee convention) ማዕቀፍን ተቀብለው ካፀደቁ ቀዳሚ አገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት። በተጨማሪ እ.ኤ.አ በ1967 የስደተኞች ፕሮቶኮል (Refugee protocole) እንዲሁም 1969 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የስደተኞች አስተዳደር ዲክላሬሽ አዋጅንም ተቀብላ አፅድቃለች:: እነዚህ ሁሉ ህጋዊ ማዕቀፎች ባሉበት ሁኔታ በተለይም ከ1950ዎቹ ጀምሮ በሶማሊያ እና በሱዳን በነበሩ ግጭቶች ተፈናቅለው የመጡ ሰዎችን ስታስተዳደር ነበር።

በዛ ወቅት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር፤ በኢትዮጵያ ፅህፈት ቤት ለመክፈት የመጡበት ጊዜ ነበር። እርሱን ተከትሎ ደግሞ በኢትዮጵያ ያሉ ሁኔታዎችን ለመደገፍ በወቅቱ የአገር ግዛት ልዩ ፅህፈት ቤት ተቋቁሞ በጋራ ሲሰራ ነበር። ይህ ጥንስስ ቀስ በቀስ ሔዶ አሁን ያለውን አገራዊ ተቋም እንዲመሰረት ሆኗል። ስለዚህ ተቋሙ በተለያየ ስያሜ በተለያዩ ተቋማት ስር ሆኖ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የነበረ ተቋም ነው። ነገር ግን እንደ ተቋም እራሱን ችሎ ሕጋዊ ሰውነት ይዞ የተቋቋመው በ2011 ዓ.ም አገራዊ ሪፎርሙን ተከትሎ ነው። በዛ ጊዜ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ በሚል በሰላም ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋም ሆኖ ተቋቁሟል።

እንደገና በ2013 ዓ.ም በወጣው የአስፈፃሚ ተቋማትን መልሶ የማቋቋሚያ አዋጅ ደግሞ ስያሜውን በመቀየር የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት በሚል ራሱን ችሎ ተቋቁሟል።

**አዲስ ዘመን፡- ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾችን በተመለከተ የምትሠሩት ሥራ ምን ይመስላል?**

**አቶ ተስፋሁን፡-** ስደት ከሚለው ጋር ተያይዞ የሚምታቱ ሶስት ዓይነት መፈናቀሎች አሉ። በቅድሚያ እነርሱን ግልፅ እናድርግ። የመጀመሪያው መፈናቀል አንድ ኢትዮጵያዊ ወይም የማንኛውም አገር ዜጋ ለትምህርት፣ ለሥራ ወይም ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ከአገሩ ወደ ሌላ አገር በሚሔድበት ጊዜ ፍልሰት (ማይግሬሽን) ይባላል። ይህ ከቀዬ መሰደድ ቢሆንም ዓላማውም ሆነ ግፊቱ መልካም ነው።

ኢትዮጵያውያን በዚህ እና በሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ከአገር ከወጡ በኋላ ሲመለሱ ከስደት ተመላሽ ይባላሉ። ሌላው ደግሞ ተፈናቃይ ነው። በጦርነት ወይም በተፈጥሮ ችግር ምክንያት ከአንድ የአገሪቷ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚደረግ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ መፈናቀል ነው። ይህ ተፈናቃይ ይባላል። ሶስተኛው ደግሞ ስደት (Refugee) የሚባለው ነው። ስደት የምንለው ከኢትዮጵያ አንፃር የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ በአገራቸው ጦርነት ወይም ግጭት በመከሰቱ እና በግላዊ ማንነታቸው በመሳደዳቸው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ስደተኞች ይባላሉ።

አሁን ለእነዚህ ስደተኞች ምላሽ መስጠት የእዚህ ተቋም ሥራ ብቻ ነው። የሚደግፍ እና በየዘርፉ አስተዋጽኦ የሚያደርግ የለም ማለት አይደለም። ለምሳሌ ፌዴራል ፖሊስ ጥበቃ ላይ ያግዛል። የክልል መንግስታት መሬት ከመስጠት ጀምሮ ፀጥታ ላይም ብዙ ያግዙናል። ሌሎችም ተቋሞች ለምሳሌ ኢሚግሬሽን የሰነድ ጉዳዮችን በተመለከተ ብዙ ያግዛል። በዋነኛነት ግን ከጥንስሱ ጀምሮ ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ የሚሰራው የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ተቋም ነው።

ውጭ ጉዳይም ሆነ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ብዙ ተቋማት የሚሰሩት ኢትዮጵያውያን ተመላሾች ላይ ነው። እኛም በተወሰነ መልኩ ብንሠራም በዋናነት የእኛ ኃላፊነት አይደለም። ስደት እና ፍልሰት ተደባልቀው ስለሚታሰቡ እና በአማርኛ ቋንቋ ደግሞ ለሁለቱም ስደት የሚል ቃል ስለምንጠቀም ብዙ ጊዜ ይምታታል እንጂ፤ የስደት ጉዳይ የዚህ ተቋም ሥራ ነው። የፍልሰት ጉዳይ በተመለከተ ደግሞ በጣም በርካታ አባላት ያሉት በርካታ ተቋማትን የሚያስተባብር እና በርካታ ሥራ የሚሠራ በብሔራዊ ደረጃ ምክር ቤት አለ። ስለዚህ እኔ መግለፅ የምችለው ስደትን ወይም Refugee የተመለከተ ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙን ለብቻው በሕግ በ2011 ዓ.ም እንዲቋቋም የገፉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ተስፋሁን፡-** ይህንን በሁለት መልኩ ማየት እንችላለን። አንደኛው በዓለም አቀፍ ደረጃ የስደተኞች ቁጥር በጣም እየገፋ በመምጣቱ ነው። በ2019 ዓ.ም የስደተኛው ቁጥር በጣም ጨምሮ ወደ 800 ሺህ የተጠጋበት ጊዜ ነበር። ከዛ በፊት በነበረው በዓለም ደረጃ የሚሠራበት ሁኔታ አልነበረም። በሌላ በኩል የስደተኛን ጉዳይ ዘላቂ በሆነ መልኩ ልማትን እና ሰብዓዊ ድጋፍን ባቀናጀ መልኩ ሁሉን አቀፍ ምላሽ መሰጠት አለበት የሚለው ከፍተኛ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር።

እ.አ.አ በ2016 ኒዮውርክ በተካሔደ ስብሰባ ላይ በጣም ከፍተኛ ተሳትፎ ተደርጎበት በዓለም ደረጃ በአገራት መሪዎች የተካሔደ ከፍተኛ ጉባኤ ነበር። የስደት ጉዳይ ዓለም አቀፍ ጉዳይ በመሆኑ ይህንን መልኩን በሚመጥን ደረጃ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል የሚል ሰፊ ውይይት ተደርጎ፤ ብዙ አቅጣጫዎችም ተቀምጠዋል። ኢትዮጵያም እንደ አገር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በ2016 በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ አማካኝነት በዘጠኝ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ቃል ገብታለች።

በቃሏ መሠረት የስደተኞች ጉዳይ አጠቃላይ ምላሽ ለመስጠት ማዕቀፍ ያስፈልገዋል የሚል አቅጣጫ ተቀምጧል። ይህንን መነሻ በማድረግ በአገራችን በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። ከእነዚህ መካከል የምላሹን ጉዳይ ሰብዓዊ ድጋፍ ብቻ ላይ ያተኮረ ሳይሆን የልማት አቅጣጫዎችንም ያማከለ እንዲሆን ማድረግን ያካተተ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለስደተኞች የሚሰጠው ምላሽ ለስደተኞች ብቻ ከሆነ ዘላቂ ስለማይሆን ለስደት ተቀባይ ማህበረሰብም ዕርዳታው ያስፈልጋል የሚል ነው።

> **ተቋሙ በተናጥል የተቋቋመበት ምክንያት አንደኛው የስደተኞች ቁጥር መጨመር፣ በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ የነበረው ትኩረት እና ኢትዮጵያም በዓለም ደረጃ የገባቻቸው ቃልኪዳኖች ጊዜያዊ ምላሽ ላይ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ መፍትሔ ላይም ያተኮሩ ስለነበሩ እነርሱን በሙሉ ባቀናጀ መልኩ ምላሽ ለመስጠት ነው**

ይህ ከፍተኛ የአቅጣጫ ለውጥ የሚያመጣ ነው። ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ስደተኞችን የሚያስተዳድሩ ክልሎች ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል፣ አፋር በኢትዮጵያ ደረጃ ራሱ በልማት ወደ ኋላ የቀሩ የሚባሉ ናቸው። እነዚህ ክልሎች ካላቸው ትንሽ ሀብት አቋድሰው ለስደተኞች የሚያካፍሉ ከሆነ፤ እነርሱንም የሚያግዝ መሆን አለበት የሚል አቅጣጫ ተቀምጧል። ኤጀንሲው በመምሪያ ደረጃ በሚሰራበት ጊዜ መጀመሪያ ሥራው ጊዜያዊ ድጋፍ ላይ ብቻ ነበር። ከጊዜያዊነት በተጨማሪ ዘላቂ ድጋፍ ለማድረግ ተቋሙ መቀየር ነበረበት። በተጨማሪ ወቅቱ በአገር ደረጃ የተቋማት ሪፎርም ሲካሔድበት ነበር። ስለዚህ ተቋማትን በአዲስ መልክ የሚያቋቁመው የአስፈፃሚ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጅ ሲወጣ፤ ከዋና መምሪያነት ወጥቶ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ እንዲወጣ ገፊ ምክንያት ሆኗል ማለት ነው።

ስለዚህ ተቋሙ በተናጥል የተቋቋመበት ምክንያት አንደኛው የስደተኞች ቁጥር መጨመር፣ በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ ደረጃ የነበረው ትኩረት እና ኢትዮጵያም በዓለም ደረጃ የገባቻቸው ቃልኪዳኖች ጊዜያዊ ምላሽ ላይ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ መፍትሔ ላይም ያተኮሩ ስለነበሩ እነርሱን በሙሉ ባቀናጀ መልኩ ምላሽ ለመስጠት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ወደ አንድ ሚሊየን የሚጠጉ ስደተኞች በኢትዮጵያ አሉ። በዋነኛነት ወደ 400ሺህ የሚጠጉት የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ናቸው። ከደቡብ ሱዳን በመቀጠል የሶማሊያ 320 ሺህ የሚጠጉ ስደተኞች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኤርትራ፣ ሱዳን እና በአነስተኛ ቁጥር ጎረቤት ካልሆኑ አገራትም ጭምር የመጡ ከ26 አገራት የተወጣጡ ስደተኞች በኢትዮጵያ ይገኛሉ። ኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች በተቋቋሙ የስደተኛ ጣቢያዎች በርካታ ስደተኞች ያሉት ጋምቤላ ሲሆን፤ በመቀጠል ሱማሌ ከዛም አፋር እንዲሁም አማራ እና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ስደተኞችን እያስተዳደሩ ያሉ ክልሎች ናቸው።

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ዓለም አቀፍ



ብሊንከን ቻይና ገብተዋል

## የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስይፋዊ ጉብኝት ቻይና ሄዱ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከቻይና ባለሥልጣናት ጋር ለሁለት ቀናት የሚዘልቅ ንግግር ለማድረግ ቤይጂንግ ገቡ። ይህ የብሊንከን ጉዞ የአሜሪካ ዲፕሎማት ወደ ቻይና ሲጓዝ ከአምስት ዓመታት ወዲህ የመጀመሪያው ያደርገዋል።

የአሜሪካ ባለሥልጣናት የጉዞ ዓላማ እጅግ ውጥረት ያየለበትን የአሜሪካ-ቻይና ግንኙነት ማረጋጋት ነው ብለዋል። ብሊንከን ይህን ጉዞ ለማድረግ አቅደው የነበረው ከአምስት ወራት በፊት የነበረ ቢሆንም ግዙፉ የቻይና ፊኛ አሜሪካ ሰማይ ላይ ከታየች በኋላ ጉዟቸውን መሰረዛቸው ይታወሳል።

ብሊንከን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እአአ 2021 መጀመሪያ ላይ ሥልጣን ከተረከቡ ወዲህ ቻይናን የጎበኙ ትልቁ የአሜሪካ ባለሥልጣን ናቸው። አሜሪካ ከብሊንከን ጉብኝት ትልቅ ውጤት እንደማትጠብቅ የገለጸች ሲሆን ይህ ጉብኝት በሁለቱ አገራት መካከል ጉልህ የሆነ ለውጥ ላያመጣ እንደሚችል ሁለቱም አገራት ያምኑበታል።

አሜሪካ የጉብኝቱ ዓላማ ሁለቱ አገራት ወደፊት ለንግግር ክፍት እንዲሆኑ እና ሰላይ ናት የተባለችው የቻይና ፊኛ በአሜሪካ የአየር ክልል መገኘቷ የፈጠረውን ውጥረት ማርገብ ነው ትላለች። በዚህ መካከል ቻይና የራሴ አንድ ግዛት አካል ነች በምትላት ታይዋን አቅራቢያ ወታደራዊ ልምምድ አድርጋለች።

የራሷ የሆነ ሕገ-መንግሥት ያላት፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የተመረጡ መሪዎች እና ከ300 ሺህ ያላነሰ የጦር ሠራዊት ባለቤት ከሆነችው ታይዋን ጋር አሜሪካ የቅርብ ግንኙነት እንዳላት ይታወቃል።

ብሊንከን በቻይና ቆይታቸው ከቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኪን ጋንግ እንዲሁም ከአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከፍተኛ ኃላፊ ዋንግ ዪ ጋር ይገናኛሉ። ብሊንከን ከፕሬዚዳንት ዢ ዢንፒንግ ጋር ስለመገናኘታቸው የተባለ ነገር የለም።

ኅዳር ወር ላይ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከዢ ጋር በባሊ ከተገናኙ በኋላ በሁለቱ ኃያላን አገራት መካከል ሊፈጠር ይችላል ተብሎ ተሰግቶ የነበረውን ‘የቀዝቃዛ ጦርነት’ ስጋት አርግቧል።

ይሁን እንጂ የሰላይዋ ፊኛ መገኘት በሁለቱ አገራት መሪዎች መካከል ይፋዊ ግንኙነትን አቀዛቅዞ ቆይቷል። በዩክሬን እየተካሄደ ስላለው ጦርነት፣ የረቀቁ የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ ውጤቶች ንግድ አለመግባባት፣ በአሜሪካ የፌንታሊን እጽ መስፋፋት እንዲሁም የቻይና የሰብዓዊ መብት አያያዝ ከብሊንከን አጀንዳዎች መካከል ይገኙበታል።

## ፈረንሳይ በማሕበራዊ ሚዲያ ሐሰተኛ ምርት የሚያስተዋውቁ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ልትቀጣ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ፈረንሳይ በማሕበራዊ ሚዲያ ገፆቻቸው ለበርካታ ተከታዮቻቸው ሐሰተኛ ምርቶች የሚያስተዋውቁ ሰዎች ላይ ዘመቻ ከፍታለች።

እኒህ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ለበርካታ ሺህ ተከታዮቻቸው የካንሰር ፈውስን ጨምሮ ሌሎች ሐሰተኛ ምርቶችን ያስተዋውቃሉ።

ፈረንሳይ አዲስ ያወጣችው ሕግ አደገኛና አሳሳች ምርት የሚያስተዋውቁ ሰዎች የገንዘብ ቅጣትና የሁለት ዓመት እስር ይጠብቃቸዋል ይላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስፋፋ የመጣውን ሐሰተኛ ምርት ማስተዋወቅ ለመግታት መንግሥት ብቻ ሳይሆን ግለሰቦችም ዘምተዋል።

የሁለት ልጆች እናት የሆነችው አድሪ የኢንስታግራም ገፅ ከፍታ እኚህን ሰዎች እያጋለጠች ነው።

አንድ ‘ሪያሊቲ ቲቪ’ ላይ የሚታወቅ ግለሰብ የካንሰር ሴሎችን ያድናል ያለውን ምርት ሲያስተዋውቅ ስትመለከት ነው ወደዚህ ሥራ የገባችው።

በተፅዕኖ ፈጣሪዎች የተጨበረበሩ ሰዎችን ለማገዝ የተቋቋመ አንድ ድርጅት አንዳንድ ሰዎች ከተታለሉ በኋላ ራሳቸውን ለማጥፋት ቃጥተዋል ይላል።

“ሰዎች ትዳራቸውን ፈተዋል፤ ቤታቸውን አጥተዋል፤ ሥራቸውንም እንዲሁ፤ ለድባቴ ተዳርገዋል” ሲሉ አቪ ኮሌክቲች የተሰኘው ድርጅት ቃል አቀባይ ለቢቢሲ ይናገራሉ።

የፈረንሳይ ፓርላማ አባሉ አርተር ዴላፖርቴ በዚህ ማጭበርበር ዘዴ ምክንያት ሰዎች እስከ 43 ሺህ ፓውንድ ድረስ አጥተዋል ይላሉ።

“ይህ ሕግ ለተጭበረበሩ ሰዎች የወጣ ነው፤ ባለሥልጣናትን ለማሳወቅ ለሠሩ ዜጎች የወጣ ነው” ሲሉ ለላይኛው የፈረንሳይ ምክር ቤት ተናግረዋል።

አድሪ፤ ይህ ጉዳይ ሀገራዊ የጤና ቀውስ ነው ትላለች። “ሰዎች ሕመም ላይ ሲሆኑ የሆነ የሚያድናቸው ነገር እንዳለ ያስባሉ። ተጨማሪ ምግብ ከካንሰር ያድነናል ብለው መድኃኒት መውሰድ ሲያቆሙ ሊብስባቸው ይችላል።”

ነገር ግን ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለቅሞ ማጋለጥ ቀላል ሥራ አይደለም። ባለፈው ዓመት አንድ ክሪፕቶ ጉቭ የተሰኘ ስም ያለው የዩቲዩብ ገፅ 300 ሰዎችን አጨበርብሮ 4 ሚሊዮን ዩሮ ይዞ እንደጠፋ ሕግ አውጪው አሪሊዬን ታሼ ይናገራሉ።

ክሪፕቶ ጉቭ፤ ክሪፕቶከረንሲ ላይ እንዴት ወጪ ፈሰስ ማድረግ ይቻላል የሚል ሐሰተኛ መመሪያ ሰጥቶ ሰዎች እንዲያምኑት በማድረግ ነው ያጭበረበረው።

ሌላኛው ፈረንሳይ ውስጥ በጣም ታዋቂ የነበረው የማጭበርበር ሂደት ሥራ ለሚፈልጉ ሰዎች 500 ዩሮ እንሰጣለን ሲል የጀመረው ነው።

ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ይህንን ሥልጠና እንዲያስተዋውቁ ጉርሻ ተሰጥቷቸው ነበር። የፈረንሳይ የኢኮኖሚ ሚኒስቴር እንደሚለው በዚህ የማጭበርበር ዘዴ ምክንያት 43 ሚሊዮን ዩሮ ጠፍቷል።


ሰዎች ዕቃ አዘው ሳይመጣላቸው ይቀራል፤ ለመዝናናት ቲኬት ቆርጠው፤ ሆቴል ተከራይተው ይታለላሉ፤ የተከለከለ ነገር ያዘለ ሻምፑ ገዝተው ፀጉራቸውን ያጣሉ።

በ2023 በተሠራ ጥናት ከ60 ተፅዕኖ ፈጣሪዎች መካከል 60 በመቶው ምርቱን ሳያጣሩ የሚያስተዋውቁ ናቸው። አሁን መንግሥት እርምጃ እየወሰደ ነው። አንዳንድ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሐሰተኛ ምርትና አገልግሎት ስላስተዋወቁ መቀጣታቸውን የሚያሳይ ፅሑፍ እንዲለጥፉ በመንግሥት ተገደዋል።

2.2 ሚሊዮን ተከታዮች ያሉት ኢላን ካስትሮኖቮ በኢንስታግራም ገፁ ቁማርና ሐሰተኛ ሥልጠና ማስተዋወቁን እንዲያምን ተደርጓል። የቀድሞ የሪያሊቲ ቲቪ ኮከብ የነበረችው ማየቫ ጌናም በአዲሱ ሕግ እንደምትስማማ ለ3.3 ሚሊዮን ተከታዮቿ ገልጻለች።

አሁን ጥያቄው የፈረንሳይ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ከአዲሱ ሕግ ጋር እንዴት ይታረቃሉ የሚለው ነው።

# ስፖርት



# ሻሸመኔ ከተማን በፕሪሚየር ሊጉ ታላቅ የማድረግ ጉዞ

ብርሃን ፈይሳ

በ2016 የውድድር ዓመት በቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ከሚታዩ አዳጊ ክለቦች መካከል አንዱ ሻሸመኔ ከተማ ነው። በሶስት ምድብ ተከፍሎ ሲካሄድ በቆየው ከፍተኛ ሊግ ቻምፒዮን ከሆኑት ክለቦች መካከል አንዱ የሆነው ሻሸመኔ ከተማ በአሰልጣኝ ጸጋዬ ወንድሙ እየተመራ ከ15 አመት በኋላ ወደ ትልቁ የውድድር መድረክ ተመልሷል።

ሻሸመኔ ከተማ ለስኬት ሲደርስ የቀድሞ ተጫዋች የአሁኑ አሰልጣኝ ጸጋዬ ትልቅ ሚና አላቸው። ወደ አሰልጣኝነት ሙያ ከገቡ በኋላ አቃቂ እና ኢትዮጵያ መድንን የመሩት እኚህ ሰው በቀጣይም ሻሸመኔ ከተማን በፕሪሚየር ሊጉ ጠንካራ ተፎካካሪ የማድረግ እቅድ አላቸው። ሻሸመኔ ከተማ በ2000 የፕሪሚየር ሊጉ ተሳታፊ የነበረ ሲሆን፤ ላለፉት 15 ዓመታት በከፍተኛ ሊግ ሲወዳደር ቆይቷል።

ባለፉት ዓመታት የከፍተኛ ሊግ ቆይታው አጥጋቢ እንቅስቃሴ ማሳየት ያልቻለውን ሻሸመኔ ከተማን የተረከቡት አሰልጣኝ ጸጋዬ፣ በራሳቸው መንገድ ተጫዋቾችን ለውድድር በማዘጋጀት ክለቡ በተሳተፈበት የሲቲ ካፕ ውድድር ጥሩ ብቃት እያሳዩ ወደ ውድድር መግባታቸውን ያስታውሳሉ።

በከፍተኛ ሊግ ላይ ከየምድባቸው አንደኛ የወጡ ክለቦች ብቻ ፕሪሚየር ሊጉን የሚቀላቀሉ እንደመሆኑ ፉክክሩ ፈታኝ እንደነበር አሰልጣኝ ጸጋዬ ያስታውሳሉ። ነገር ግን የክለቡ ግብ ፕሪሚየር ሊጉን መቀላቀል እንደመሆኑ ለውድድሩ ምን ያስፈልጋል እንዲሁም በመጀመሪያውና ሁለተኛው ዙር ምን በምን መልኩ መዘጋጀት ይገባል የሚለውን ከልምድ ተነስቶ በማቀድ እንደተንቀሳቀሱ አሰልጣኙ ይናገራሉ። በዚህም ክለቡ በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት በመሪነት ቢቆይም ዙሩን ያጠናቀቀው ግን ከአዲስ አበባ ከተማ ጋር በእኩል ነጥብ ነበር። በሁለተኛው ዙር ደግሞ ጥቂት አዳዲስ ተጫዋቾችን ወደ ክለቡ በማካተት እንዲሁም በነበሩባቸው ድክመቶች ላይ በመስራት መሪነቱን አጠናክሮ ቀጥሎ አራት ጨዋታ እየቀረው ቻምፒዮን መሆኑንና ወደ ፕሪሚየር ሊጉ መመለሱን በጊዜ እንዳረጋገጠ ያስረዳሉ።




ለዚህም አንዱ ምክንያት የቡድኑ አባላት በተመሳሳይ ስሜት እና ዓላማ ተግባብተው መጫወታቸው እንደነበር አሰልጣኝ ጸጋዬ ይናገራሉ። "በጥንቃቄና አብረዋቸው ከሚጫወቷቸው ቡድኖች ጋር በምን መልኩ መቅረብ እንደሚገባቸው አውቀው ከመገኘታቸው በላይ ተጫዋቾቹ ቆራጥ ነበሩ" የሚሉት አሰልጣኙ ጸጋዬ፣ ከፍተኛ ሊግ እጅግ ጠንካራና ተደጋጋሚ ጨዋታ ያለበት ውድድር ቢሆንም ሻሸመኔ ከተማ በሊጉ ታሪክ ብዙ ጨዋታ እየቀረው ማለፉን ያረጋገጠ ቡድን በመሆንም ታሪክ እንደሰራ ያስረዳሉ።

በዚህም ሂደት ከተጫዋቾች ባሻገር የስልጠና ቡድኑ እንዲሁም የክለቡ አመራሮች የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነበር። ክለቡ በከተማዋ ከንቲባ የሚመራ እንደመሆኑ በልምምድ ወቅትም ይሁን በተለያዩ ጊዜያት ከንቲባው መገኘታቸውና ማበረታታቸው ትልቅ እገዛ ማድረጉን አሰልጣኙ ተናግረዋል።

በከፍተኛ ሊግ ጠንካራ የነበሩ ቡድኖች ወደ ፕሪሚየር ሊጉ ቢያድጉም ተወዳዳሪ መሆን ባለመቻላቸው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደመጡበት ሲመለሱ ይስተዋላል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ሻሸመኔ ከተማ ተመሳሳይ ነገር እንዳይገጥመው ዝግጅቱን ከወዲሁ መጀመሩን ጠቁመዋል። አሰልጣኝ ጸጋዬ እንደተለመደው ሳይሆን በሊጉ ክስተት የሆነ ቡድን ይዘው ለ2016 የውድድር ዓመት እንደሚቀርቡ እምነት አላቸው።

አሰልጣኝ ጸጋዬ የውድድር ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ሻሸመኔ ከተማን ሲረከቡ ክለቡን ለፕሪሚየር ሊግ ለማብቃት ቃል መግባታቸውን በማስታወስ በዚህም ስኬታማ መሆናቸውን ይናገራሉ። በቀጣይም በዋናው ሊግ ጠንካራ ተፎካካሪ ሆነው ለመቅረብ ከወዲሁ እየሰሩ ይገኛሉ። ለዚህ እንዲረዳቸውም ከውድድሩ መጀመሪያ አንስቶ ጠንካራ ዝግጅት ለማድረግ አስበዋል። ተፎካካሪ ክለቦች ስላሉበት ሁኔታም ዳሰሳዊ ጥናት እያደረጉ ይገኛሉ።

ከዚህ ባለፈ ቡድናቸውን በወጣት ተጫዋቾች ላይ የተመሰረተ በማድረግ በፕሪሚየር ሊጉ ክስተት የሚሆን ቡድን የመገንባት ሃሳብ አላቸው። ለሊጉ ድምቀት ይሆናል ያሉትን የክለቡ ደጋፊዎችን ይዘውም ውድድሩን የሚመጥን ተፎካካሪ ቡድን እንደሚሰሩ ትልቅ ተስፋ ሰንቀዋል።

አሰልጣኙ ያሰቡትን ለማሳካት የመጀመሪያው ዓመት ዕቅዳቸው ክለቡን በተረጋጋ ሁኔታ በሊጉ እንዲቆይ ማድረግ ነው። ያላቸውን ጊዜ ተጠቅመውም ቡድኑን በጥሩ መንገድ ገንብተው ቃላቸውን በመተግባር ለመለወጥ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ለክለቦች በፕሪሚየር ሊጉ ላይ ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ለመዝለቅ በዋናነት አስፈላጊ የሆነው ጉዳይ ፋይናንስ ነው። የክለቡ አመራሮችም ይህንን የሚገነዘቡ በመሆኑ በዚህ ዓመት ሲያደርጉ በቆዩት መጠን በጠንካራ ጥረትና ክለቡን ከሚወዱት አካላት እንዲሁም ከተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ክለቡን ይደግፋሉ የሚል ዕምነት እንዳላቸው አሰልጣኙ ተስፋ አድርገዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞም የከተማዋን ከንቲባ ጨምሮ የክለብ አመራሮች፣ የከተማው እግር ኳስ ፌዴሬሽን እንዲሁም ቡድኑን ሲደግፉ ለነበሩ አካላት ላደረጉት እገዛ አሰልጣኙ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።